

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ የአፋር እና የአማራ ክልሎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ የተደረገ ምርመራ ሪፖርት

አባሪዎች

መጋቢት 2 ቀን 2014 ዓ.ም.

ማውጫ

አባሪዎች ..... Error! Bookmark not defined.
አባሪ 1 1
ኢሰመኮ ምርመራ ያደረገባቸው እና የትግራይ ኃይሎች በአፋር እና በአማራ ክልል 1
..... 5
አባሪ 2 6
የግጭት ተሳታፊዎች ዝርዝር 6
አባሪ 3 8
ከኢሰመኮ ለትግራይ ክልል እንዲላክ የተዘጋጀ ደብዳቤ 8
አባሪ 4 14
ከኢሰመኮ ለኢ.ፌ.ድ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ 14
አባሪ 5 17
ከኢሰመኮ ለትምህርት ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ 17
አባሪ 6 19
ከኢሰመኮ ለፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የተላከ ደብዳቤ 19
አባሪ 7 21
ከኢሰመኮ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተላከ ደብዳቤ 21
አባሪ 8 23
ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ 23
አባሪ 9 25
ከጤና ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ 25
አባሪ 10 29
ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ 29
አባሪ 11 43
ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ መልስ 43
አባሪ 12 44
ከፌዴራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የተሰጠ መልስ 44

አባሪ 1

ኢሰመኮ ምርመራ ያደረገባቸው እና የትግራይ ኃይሎች በአፋር እና በአማራ ክልል

ውጤታማ ቁጥጥር (Effective Control) የነበራቸው አካባቢዎችና የጊዜ ሰሌዳ


አፋር ክልል		
ዞን	**ወረዳ/ቀበሌ**	**የውጤታማ ቁጥጥር ጊዜ**
ፈንቲ ረሱ ዞን	ያሎ ወረዳ	ከሐምሌ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጳጉሜ 01 ቀን 2013 ዓ.ም.
	እዋ ወረዳ	ከሐምሌ 13 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጳጉሜ 5 ቀን 2013 ዓ.ም.
	አውራ ወረዳ (ደራይቱ ከተማ)	ከሐምሌ12 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጳጉሜ 4 ቀን 2013 ዓ.ም.
	ጉሊና ወረዳ (ጋሊኮማ ቀበሌ)	ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. -መስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም.
ኪልበቲ ረሱ ዞን	ኡደሌዳባ እና ማያራሉ	ከጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. - ጎዳር 18 ቀን 2014 ዓ.ም.
	አዳ አር ወረዳ ዋአንቱና ፉርሳ ቀበሌ ካሳጊታ ከተማ	ከጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. -ጎዳር 18 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ጭፍራ ከተማ	ከጥቅምት 07 ቀን 2014 ዓ.ም. - ጎዳር 19 ቀን 2014ዓ.ም.
	ቡርቃ ቀበሌ	ከጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. - ጎዳር 18 ቀን 2014 ዓ.ም.


አማራ ክልል		
ዞን	**ወረዳ**	**የውጤታማ ቁጥጥር ጊዜ**
ሰሜን ጎንደር ዞን	ደባርቅ ወረዳ፣ ድብ ባህር ንዑስ ወረዳ፡-	ከነሐሴ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጳጉሜ 03 ቀን 2013 ዓ.ም.
	ደባርቅ ወረዳ፣ ቦላ ቀጠና አዲጋግራ፣ አብርሃም እና አዳጋት ቀበሌዎች	ከነሐሴ 12 እስከ 29 ቀን 2013 ዓ.ም.


	ዳባት ወረዳ ጭና ቀበሌ	ከነሐሴ 24 እስከ 29 ቀን 2013 ዓ.ም.
	በአዲአርቃይ ወረዳ ዛሪማ ንዑስ ወረዳ	ከሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም. -ጳጉሜ 2 ቀን 2013 ዓ.ም.
ሰሜን ወሎ ዞን	ጋሸና ከተማ	1. ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. - ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. 2. ከነሐሴ 16 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም. 3. ከጥቅምት 6 ቀን 2014 ዓ.ም. - ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. 4. ከታኅሣሥ 2 ቀን 2014 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም.
	አርቢት ከተማ	1. ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. - ነሐሴ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. 2. ከነሐሴ 16 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም. 3. ከጥቅምት 6 ቀን 2014 ዓ.ም. - ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. 4. ከታኅሣሥ 2 ቀን 2014 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ዋድላ ወረዳ ሐሙሲት ከተማ	ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 9 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ላስታ ወረዳ የዳቦ ከተማ	ከሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ላስታ ወረዳ ድብኮ ከተማ	1. ከሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ.ም. - ኅዳር 22፣ 2014 ዓ.ም. 2. ከታኅሣሥ 4፣2014 ዓ.ም. እስከ ታኅሣሥ 8፣ 2014 ዓ.ም.
	ላስታ ወረዳ የላሊበላ ከተማ	1. ከሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. - ኅዳር 22 ቀን 2014 ዓ.ም. 2. ከታኅሣሥ 3 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ
	ላስታ ወረዳ ሹምሽሃ (የላሊበላ ኤርፖርት	1. ከሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. - ኅዳር 21 ቀን 2014 ዓ.ም. 2. ከታኅሣሥ 04 ቀን 2014 ዓ.ም. - 09 ቀን 2014 ዓ.ም.

	የሚገኝበት ቀበሌ)	
	መቄት ወረዳ ደብረዘቢጥ ቀበሌ	ከሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. - መስከረም 1 ቀን 2014 ዓ.ም.
	መርሳ ከተማ	ከነሐሴ 3 ቀን 2013 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ወልዲያ ከተማ	ከነሐሴ 3 ቀን 2013 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 9 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ጣጃ ከተማ	ከሐምሌ 7 ቀን 2013 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 7 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ፍላቂትና ገረገራ ከተማ	ከነሐሴ 29 ቀን 2013 ዓ.ም. - ጳጉሜ 5 ቀን 2013 ዓ.ም.
አማራ ክልል		
ዞን	**ወረዳ/ ቀበሌ**	**የውጤታማ ቁጥጥር ጊዜ**
ደቡብ ወሎ ዞን	አምባሰል ወረዳ ውጫሌ ከተማ፡-	ከነሐሴ 3 ቀን 2013 ዓ.ም. - ታኅሣሥ 8 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ወራባቡ ወረዳ	ከነሐሴ 24-30 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ተሁለደሬ ወረዳ	ከነሐሴ 27-29 ቀን 2013 ዓ.ም.
	ሀይቅ ከተማ	ከጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. -ጎንደር 28 ቀን 2014ዓ.ም.
	ደሴ ከተማ	ከጥቅምት 20 ቀን 2014 ዓ.ም. -ጎንደር 28 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ኮምቦልቻ ከተማ	ከጥቅምት 21 - ጎንደር 25 ቀን 2014 ዓ.ም.
ሰሜን ሸዋ ዞን	**አጣዬ ከተማ**	ከጎንደር 5 ቀን 2014 - ጎንደር 22 ቀን 2014 ዓ.ም.
	ካራ ቆሬ ቀበሌ	ከጥቅምት 28 ቀን 2014 - ጎንደር 24 ቀን 2014
	መንዝ ጌራ ምድር ወረዳ መሀል ሜዳ ከተማ	ከጎንደር 9 - 22 ቀን 2014 ዓ.ም.
	መዘዞ ንዑስ ወረዳ	ከጎንደር 14 - 21 ቀን 2014 ዓ.ም.

	ቀወት ወረዳ የለን ቀበሌ አነስተኛ ከተማ እና ሸዋ ሮቢት	ከጎዳር 9 - 22 ቀን 2014 ዓ.ም.
	አንጾኪያ ገምዛ ወረዳ	ጎዳር 23 ቀን 2014 ዓ.ም. (ለአንድ ቀን ብቻ)
ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን	ኬሚሴ ከተማ	ከጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም. እስከ ጎዳር 25 ቀን 2014 ዓ.ም. (ከአነግሸኔ ሀይሎች ጋር በመሆን)
	ሰንበቱ ከተማ	ከጎዳር 5 — 24 ቀን 2014 ዓ.ም. (ከአነግ ሸኔ ኃይሎች ጋር በመሆን)


አፋር ክልል
አፋር ክልል (ፈንቲደሱ ዞን)
አፋር ክልል (ኪልሰቲደሱ ዞን)
አማራ ክልል (ሰሜን ጎንደር ዞን)
አማራ ክልል (ሰሜን ወሎ ዞን)
አማራ ክልል (ደቡብ ወሎ ዞን)


አፋር ክልል
አማራ ክልል (ሰሜን ወሎ ዞን)


አፋር ክልል
አማራ ክልል (ሰሜን ጎንደር ዞን)
አማራ ክልል (ሰሜን ወሎ ዞን)
አማራ ክልል (ደቡብ ወሎ ዞን)
ሰሜን ሸዋ ዞን
አጣዬ ከተማ
ካራ ቆሬ ቀበሌ
መንገዝ ጌራ ምድር ወረዳ መህል ሚዳ ከተማ
መሸሀ ንፁህ ወረዳ
ቀወት ወረዳ የለን ቀበሌ አነስተኛ ከተማ እና ሸዋ ሮቢት
አንጾኪያ ገምዛ ወረዳ (ሰሜን ሸዋ ዞን)
አርሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን (ከአነግ ሸኔ ሀይሎች ጋር በ...
Derek' Amba
Alala
Lugama
Neded
Were Ilu
Beret Wenz
Gich'uma
Rabel
ጊሼ ራቤል
K'oseru
Dayer
Ayzosh Amora
Darat
Iruf Kolemo
Debora
Guracha
Zerk'ami
Degolo
Ank'elafit
Amerguya
Bar Meda
Gidim
Geba
Ak'afe
Ambersha
Gifreye
Surafel
Kelidoro
Indo
Gomen Amba
Gerbe
Demk'a
Termaber
ጣርማበር
Gino
Kewet
ቀወት
Gimb
Molale
Jewaha
Yimwota
Imbus Amba
Jihur
Dengeze
Ch'aso
Jer
Sasit
Sela Dingay
Golele
Robit
Abaye Atir
Dabita
Dugudu
Gora
Gore
Dewe
ደወ
Shonke
Artuma
Tinishu Rebi
Fursi
Senbete
Gifreye
Kelidoro
Gerbe
Gimb
Jewaha

አባሪ 2

የግጭት ተሳታፊዎች ዝርዝር

የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት መሰረት የተቋቋመ የሀገሪቱ የጦር ሀይል ሲሆን የምድር፣ የአየር እና የባህር ኃይሎችን ያጠቃልላል። የመከላከያ ሚኒስትር ሲቪል አመራር የሚሰጥበት ሲሆን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የጦሩ ጠቅላይ አዛዥ ናቸው።

ፌዴራል ፖሊስ፡ የፌዴራል መንግሥቱ መደበኛ የፖሊስ ኃይል ሲሆን ፌደራል መንግስቱን የሕግ ማስከበር፣ ወንጀል የመከላከል እና የምርመራ ስራዎችን ያከናውናል። በተጨማሪም በመላ ሀገሪቱ ለሚገኙ የፌዴራል ተቋማት እና ንብረቶች የደህንነትን ጥበቃ አገልግሎት ያከናውናል።

የትግራይ ኃይሎች፡ በጦርነቱ ወቅት የተሳተፉትን የትግራይ ልዩ ሀይል፣ ፖሊስ፣ ሚሊሺያ እና ሌሎች አባላቶቹን ጨምሮ ራሱን ትግራይ መከላከያ ሠራዊት በማለት የሚጠራውን ወታደራዊ ኃይል ያጠቃልላል።

የትግራይ ልዩ ኃይል፡ በክልሉ የሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮችን ለመቆጣጠር የተቋቋመና የተለየ ስልጠና እና ትጥቅ ያለው ኃይል ነው። አባላቶቹ በክልሉ መንግሥት የሚመለመሉ ሲሆን ለክልሉ ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆነ የራሱ አዛዥ አለው።

የትግራይ ክልል ፖሊስ፡ በክልሉ የሕግ ማስከበር፣ ወንጀልን የመከላከል እና የማጣራት ሃላፊነት የተጣለበት የትግራይ ክልል መደበኛ የፖሊስ ኃይል ነው።

የትግራይ ክልል ሚሊሺያ፡ በመደበኛ ጊዜ በግብርና ወይም በሌላ ስራ የተሰማሩ ሲቪል ሰዎች ሲሆኑ በገጠር አካባቢዎች የፖሊስ ስራ በመስራት የአካባቢያቸውን ሰላም ለማስጠበቅ የተደራጁ በጦርነት ጊዜ ደግሞ ወደ ግንባር የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ሚሊሺያዎች የክልሉ አስተዳደርና የጸጥታ መዋቅር አካል ሲሆኑ በየእርከኑ ሚሊሺያዎችን የሚያስተባብሩ የሚሊሺያ ጽሕፈት ቤቶች አሉ። ከክልሉ መንግሥት የተወሰነ ወታደራዊ ስልጠና እና የደንብ ልብስ የሚያገኙ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከክልሉ መንግሥት የሚሰጥ የጦር መሳሪያ ወይም የግላቸውን መሳሪያ ይጠቀማሉ።

ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ሕወሃት)፡ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገዢ ፓርቲ የነበረ ሲሆን፤ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኛ ድርጅትነት ፈርጆታል።

የአማራ የፀጥታ ኃይሎች፡ በጦርነቱ ወቅት የተሳተፉትን የአማራ ክልል ልዩ ሀይል፣ ፖሊስ፣ ሚሊሺያ እና ፋኖን ጨምሮ ሌሎች በአማራ ክልል አማካኝነት የተደራጁ ወታደራዊ አካላትን ያጠቃልላል።

የአማራ ልዩ ኃይል፡ በክልሉ የሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮችን ለመቆጣጠር የተቋቋመና የተለየ ስልጠና እና ትጥቅ ያለው ኃይል ነው። አባላቶቹ በክልሉ መንግሥት የሚመለመሉ ሲሆን ለክልሉ ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆነ የራሱ አዛዥ አለው።

አማራ ክልል ፖሊስ፡ በክልሉ የሕግ ማስከበር፣ ወንጀልን የመከላከል እና የማጣራት ሃላፊነት የተጣለበት የአማራ ክልል መደበኛ የፖሊስ ኃይል ነው።

የአማራ ክልል ሚሊሺያ፡ በመደበኛ ጊዜ በግብርና ወይም በሌላ ስራ የተሰማሩ ሲቪል ሰዎች ሲሆኑ በገጠር አካባቢዎች የፖሊስ ስራ በመስራት የአካባቢያቸውን ሰላም ለማስጠበቅ የተደራጁ በጦርነት ጊዜ ደግሞ ወደ ግንባር የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ሚሊሺያዎች የክልሉ አስተዳደርና የጸጥታ መዋቅር አካል ሲሆኑ በየእርከኑ ሚሊሺያዎችን የሚያስተባብሩ የሚሊሺያ ጽሕፈት ቤቶች አሉ። ከክልሉ መንግሥት የተወሰነ ወታደራዊ ስልጠና እና የደንብ ልብስ የሚያገኙ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከክልሉ መንግሥት የሚሰጥ የጦር መሳሪያ ወይም የግላቸውን መሳሪያ ይጠቀማሉ።

ፋኖ፡ የአማራ ተወላጅ የሆኑ በአብዛኛው ወጣት ታጣቂዎችን የያዘ ሲሆን ከአማራ የፀጥታ ኃይሎች ጋር አብረው የሚታገሉ ኃይሎች ናቸው። አንዳንዶቹ መደበኛ አደረጃጀት ያላቸው ሲሆን በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተመላከቱት በሙሉ መደበኛ የሆነ አደረጃጀት አላቸው ሊባል አይችልም።

የአፋር የፀጥታ ኃይሎች፡ በጦርነቱ ወቅት የተሳተፉትን የአፋር ክልል ልዩ ሀይል፣ ፖሊስ እና ሚሊሺያን ጨምሮ ሌሎች በአፋር ክልል አማካኝነት የተደራጁ ወታደራዊ አካላትን ያጠቃልላል።
የአፋር ልዩ ኃይል፡ በክልሉ የሚፈጠሩ የፀጥታ ችግሮችን ለመቆጣጠር የተቋቋመና የተለየ ስልጠና እና ትጥቅ ያለው ኃይል ነው። አባላቶቹ በክልሉ መንግሥት የሚመለመሉ ሲሆን ለክልሉ ፕሬዝዳንት ተጠሪ የሆነ የራሱ አዛዥ አለው።

አፋር ክልል ፖሊስ፡ በክልሉ የሕግ ማስከበር፣ ወንጀልን የመከላከል እና የማጣራት ሃላፊነት የተጣለበት የአፋር ክልል መደበኛ የፖሊስ ኃይል ነው።

የአፋር ክልል ሚሊሺያ፡ በመደበኛ ጊዜ አርብቶ አደሮች ወይም በግብርና ወይም በሌላ ስራ የተሰማሩ ሲቪል ሰዎች ሲሆኑ በገጠር አካባቢዎች የፖሊስ ስራ በመስራት የአካባቢያቸውን ሰላም ለማስጠበቅ የተደራጁ በጦርነት ጊዜ ደግሞ ወደ ግንባር የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ሚሊሺያዎች የክልሉ አስተዳደርና የጸጥታ መዋቅር አካል ሲሆኑ በየእርከኑ ሚሊሺያዎችን የሚያስተባብሩ የሚሊሺያ ጽሕፈት ቤቶች አሉ። ከክልሉ መንግሥት የተወሰነ ወታደራዊ ስልጠና እና የደንብ ልብስ የሚያገኙ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ከክልሉ መንግሥት የሚሰጥ የጦር መሳሪያ ወይም የግላቸውን መሳሪያ ይጠቀማሉ።

የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት (የኦነግ ሸኔ ኃይሎች)፡ መንግሥት እና ሰዎች በተለምዶ ኦነግ ሸኔ በማለት የሚጠራቸው፤ ራሳቸውን የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት በማለት የሚጠሩ የራሳቸው መደበኛ አደረጃጀት እና አመራሮች ያሏቸው የታጠቁ ኃይሎች ናቸው።

አባሪ 3

ከኢሰመኮ ለትግራይ ክልል እንዲላክ የተዘጋጀ ደብዳቤ



ቁጥር ያ/ሰመኮ/ክ.ጉ/148/2014
Ref. No. 25 ጥር 2014
ቀን Date
ስልክ Tel. 011-5-504031
ፋክስ Fax 011-5-504125
ፖ.ሣ. ቁጥር P.O Box 1165
ኢ-ሜይል E-mail hrcom@ethionet.et
አዲስ አበባ Addis Ababa

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ
የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ጉዳዩ፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመጠየቅ፣


የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 ((በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ስሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ክትትል እና ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ዕቤት ጋር በጋራ በመሆን የፌደራል መንግስት ኃይሎች ከትግራይ ክልል አስከመጡበት ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳዮች ላይ ምርመራ በማድረግ የጋራ ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

ኮሚሽኑ ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ የተፈፀሙና በተለይም ግጭቱ ቀጥሎ በተስፋፋባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ለማካሄድ በተለያዩ ጊዜያት የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት ምርመራ አድርጓል።

ኮሚሽኑ ያካናወነው ምርመራ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ዘዴዎችን በመከተል ከወንጀለኝነት በወዳ መልኩ በገለልተኝነት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። የምርመራው ዘዴም በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉም አካላት ተፈፀሙ በተባሉት ጥሰቶች ላይ ምላሽ እና ማስረጃ እንዲሰጡ ማድረግን ይጨምራል።


ስለሆነም በተደረገው ምርመራ መሰረት የተለዩትን ሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎችና አጠቃላይ የነገሩን ሁኔታ በሚመለከት የክልሉ መንግስት ምላሽ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን በዚህ ደብዳቤ አባሪነት የሰነን መሆኑን አየገለፅን፣ የአናንተን ምለሽ እና አስተያት በሪፖርታችን ለማካተት ይቻል ዘንድ ምላሻችሁን ይህ ደብዳቤ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 የስራ ቀናት ውስጥ እንድትልኩልን በማክበር እንጠይቃለን።

ሰብአዊ መብቶች የማይገሠሡ፣ የማይሸራረፉ እና ሁሉ- አቀፍ
Human Rights are Inalienable, Indivisible and Univ



ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በኢሜል yibekal.gizaw@ehrc.org ስ.ቁ :- 09 11 81 70 02 ወይምኢሜል manyawkal.mekonnen@ehrc.org ስ.ቁ :-09 11 62 11 23 ኢሜል mesganaw.mulugeta@ehrc.org ስ.ቁ:- 09 11 10 57 71 ማነጋገር ይቻላል።

[redacted]



ለትግራይ ክልል የተዘጋጀ የጥያቄ መዘርዝር

1. አጠቃላይ

- የትግራይ ኃይሎች የእዝ መዋቅር አጠቃላይ እይታ (ልዩ ኃይል፣ ፖሊስ፣ ሚሊሻ፣የወጣት ቡድኖች) እና አደረጃጀት ምን ይመስላል
- የትግራይ ኃይሎች የሚጠቀሟቸው የደንብ ልብስ አይነቶች
- የትግራይ ኃይሎች፣ ከሌሎች ኃይሎች ጋር ያላቸው ግንኙነትና የእዝ ሰንሰለት (ሽኹ፣ የእገው ነባ አውጪ፣ የቅማንትና የቤኒሻንጉል ቡድኖች)
- የትግራይ ኃይሎች ወደ አማራና አፋር ክልሎች ገብተው ቦታዎችን ስለተቆጣጠሩበት ሁኔታ፣ ተቆጣጥረዋቸው የቆዩዋቸው ቦታዎችና የቆዩባቸው ጊዜያት፣ (date and duration of effective control) በወረዳ ወይም ከተማ ደረጃ ሊገለጽ ይችላል፣

2. ዝግጁነት፣ ስነምግባር ደንብ እና አያያዝ

- የትግራይ ኃይሎች እና አመራሩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግን ለመተግበር ስላለው ዝግጁነት፣ የወሰዱት ስልጠና እና የተሄደ የስነ-ምግባር ደንብ ስለመኖሩ?
- ከስምሪታቸው በፊት ለሲቪሎች ስለሚደረግ ጥበቃ፣ ጥንቃቄ ስለመውሰድና ስለተመጠጠኝነት ወሰዱት ስልጠና እና ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
- የተማረኩ የመከላከያ ሰራዊት እና ሱሰኞች በጦርነቱ ተሳትፎ የነበራቸው ኃይሎች ብዛት እና የአያያዝ ሁኔታ፣ የህክምና እርዳታን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶች ሁኔታ?


3. የሲቪል አስተዳደርን በተመለከተ

- የትግራይ ኃይሎች በአማራና አፋር ክልሎች ተቆጣጥረዋቸው በቆዩዋቸው ቦታዎች የነበረው የሲቪል አስተዳደር (ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ) ሁኔታ
- የሲቪል አስተዳደሩ የትግራይ ኃይሎች ጋር ስላለው ግንኙነት
- በእነዚህ አካባቢዎች የሕግ ማስከበር፣ የፍትህና የዳኝነት ስርአቱ የነበረበት ሁኔታ፣

4. የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች

የትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር የሰብአዊ መብቶች እና ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ተፈፅመባቸዋል ተብለው የተለዩት የሚከተሉትን ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እና ማስረጃዎች እንዲቀርቡ፣

4.1. የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥር ስር በነበሩ እና ከሚሸሹ ምርመራ ባደረገባቸው አካባቢዎች በህወሐት አባላት ላይ በታጣቂዎች ስተፈጸሙ ግድያዎች መቀጣጫ እንዲሆን በሚል፣ ለመንግስት መረጃ ሰጪ ወይም ሰላይ ናቸው (በተለይ የአዕምሮ ህመማንን)፤ የመከላከያ ሰራዊት፣ ፋኖ፣ ሚሊሻ ወይም ታጣቂ አባልናችሁ ወይም



የነዚህ አባል የሆኑ ሰዎች ቤተሰብ ናችሁ ንብረት ለመስጠት ወይም ለፍተሻ ለመተባበር ፍቃደኛ አይደሉም ወይም ለመገዳደር ምክረዋል በሚል፣ በመንገድ ላይ ሲንቀሳቀሱ በመገኘታቸው እና ለገዢው ባልታወቁ ሌሎች ምክንያቶች የተፈጸመ የሲቪል ሰዎች ግድያዎች የደረሱ የአካል ጉዳቶች

- በደቡብ ወሎ ዞን የተሁለደሬ ቀበሌ 017 በኅሐሴ 28፣ 2013 ዓ.ም የአካባቢው ነዋሪዎችን፣ ሚሊሻ ወይም ፖሊስ ናችሁ፣ በማለት የትግራይ ኃይሎች ድብደባ ካደረሱባቸው በኋላ ከመከከላቸው 1 ነዋሪን በጥይት ተኩሰው የገደሉ ስለመሆኑ፣
- በአፋር ክልል ጥቅምት 22/2014 ዓ.ም አደአር ወረዳ ቡርቃ ቀበሌ የተገደሉ ሁለት ሰዎች፣ ጥቅምት 07/ 2014 እና 24/ 2014 ዓ.ም በጭፍራ ከተማ የተገደሉ የአእምሮ ህመም ያለባቸው ግለሰቦች እና በከተማው ሲቪል ሰዎች ላይ የደረሱ ድብደባዎች፣ ጥቅምት 24/2014 ዓ.ም ከጥዋቱ 3፡00 ሰዓት ላይ ካሳጊታ ከተማ አትኩማ አከባቢ ሁለት የዘጠኝ ዓመትና የ18 ዓመት ሴት ልጆች ውሃ ለመቅዳት ወደ አስ ኢላ ወንዝ በሄዱበት ወቅት የተገደሉ፣
- በተወት ወረዳ የለን ቀበሌን የትግራይ ታጣቂዎች እንደተቆጣጠሩ የአካባቢው የሚሊሻ ኃይል ውጊያ ገጥሞ በህውኃት ታጣቂዎች ላይ ሞት እና ጉዳት በማድረሱ ምክንያት ይህንን ለመበቀል በሚል ህዳር 10/2014 ዓ.ም ከ12 እስከ 55 ዓመት የሚሆናቸው 20 ሲቪል ሰዎችን በጥይት ደብድበው መገደላቸው

4.2. የትግራይ ኃይሎች በተለያዩ አካባቢዎች ባደረጓቸው ውጊያዎች የነበሩ የከባድ መሳሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት በጦርነት ሂደት ወታደራዊ ዓላማ ጥቃት በሚፈጸምበት አካባቢ መኖሩን የማረጋገጥ፣ የተመጣጣኝነት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰዳቸውን በማያሳይ አግባብ በተፈጸሙ የከባድ መሳሪያ ጥቃቶች ምክንያት የሞቱ እና ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲቪል ሰዎች መኖራቸው፣ በተለይም ከዚህ በታች በተረዘሩት ስፍራዎች እና ክስተቶች ወቅት የነበረው የወታደራዊ ኢላማ እና በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት ላለማድረስ እና ሲቪል ሰዎችን ለመለየት የተደረጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች በሚመለከት ማብራሪያ፣ በጥቃቶቹም የደረሱት ተጓዳኝ ጉዳቶች ቢዘረዘሩ፣

- ሐምሌ 9/2013 ዓ.ም በአፋር ክልል በያሎ ወረዳ የትግራይ ኃይሎች ወደ ጎቢ-ዳራ ከተማ በተኮሰው ከባድ መሳሪያ በመኖሪያ ቤታቸው የነበሩ 3 ሲቪል ሰዎች ስለመገደላቸው
- ሐምሌ 13/2013 ዓ.ም አዋ ወረዳን ለመቆጣጠር የትግራይ ኃይሎች ከአሰፋዳ ተራራ ላይ ወደ አሰሌ ሱብላ ከተማ ከባድ መሳሪያ ተኩሰው 6 ሲቪል ሰዎች ስለመገደላቸው
- በአማራ ክልል ሐምሌ 16፣ 2013 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎች የከባድ መሳሪያ ወደ አዲ አርቃይ ከተማ በመተኮስ የአንድ ቤተሰብ አባል እና ጎረቤቶች የሆኑትን የ6 ወር ጨቅላ ህጻን፣ የ5 ዓመት ህጻን እና የ60 ዓመት እማሆይን ጨምሮ ወንድ 3 ሴት 3 በድምሩ 6 ነዋሪዎችን የተገደሉ ስለመሆኑ፣ በዚሁ ጥቃት አብረው የነበሩ 2 ወንድ እና 1 ሴት ድምር 3 ሰዎችን ስለመቁሰላቸው
- የትግራይ ኃይሎች ሐምሌ 28/2013 ዓ.ም ከሌሊቱ 9:00 ላይ በጉሊና ወረዳ፣ ጋሊኮማ ቀበሌ በሚገኙት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ

ውስጥ በነበሩት ሲቪል ሰዎች ላይ በክባድ መሳሪያዎች የታዝዘ ጥቃት በመፈፀም በጋሊኮማ ትምህርት ቤት ላይ በተተኮሰው ክባድ መሳሪያ በተነሳው እሳት ምክንያት ለተፈናቀሉ ሰዎች በእርዳታ የመጣ ምግብ የተከማቸበት መጋዘን ውስጥ ተኝተው የነበሩ 8 ሲቪል ሰዎች ተቃጥለው ስለመሞታቸው

- ከነሐሴ 14/2013 ዓ.ም ጀምሮ በበርሀሌ ወረዳ፣ አላ ቀበሌ በሚገኙ ሶስት መንደሮች (ኩሱርቱ፣ አሰዳ እና አድአርዋ) የትግራይ ኃይሎች ባደረሱት በክባድ መሳሪያ የታዝዘ ጥቃት 13 ሲቪል ሰዎች ስለመሞታቸው
- ሐምሌ 11/2013 ዓ.ም በያሎ ወረዳ የትግራይ ኃይሎች ባደረሱት የክባድ መሳሪያ ጥቃት አንድ የ28 ዓመት ወጣት ወንድ በመኖሪያ ቤቱ አንዳለ የሰውነት አካሉ ተቆራርጦ ስለመሞቱ
- ሐምሌ 12/2013 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎች በአውራ ወረዳ ውጊያ ካካሄዱ በኋላ ሐምሌ 13/2013 ዓ.ም የወረዳው ዋና ከተማ የሆነውን ደራይቱን የተቆጣጠሩ ሲሆን በዚሁ ከተማ የትግራይ ኃይሎች በተፈጸመ ጥቃት 7 ሲቪል ሰዎች መገደላቸውን እና 5 ሲቪል ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱ
- ቢሐምሌ 28/2013 ዓ.ም በጋሊኮማ ቀበሌ የደረሰው የክባድ መሳሪያ ጥቃትን በመሸሽ ወደ ወናሳ ሜዳ ሲሮጡ በነበሩ ሲቪል ሰዎች ላይ በደረሰ ጥቃት 23 ሲቪል ሰዎች ስለመሞታቸው
- በአጠቃላይ ጉሊና ወረዳ፣ ጋሊኮማ ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች በደረሰው ጥቃት 107 ሲቪል ሰዎች ስለመገደላቸው
- የትግራይ ኃይሎች የበረሃሌ ወረዳን ተቆጣጥረው በቆዩበት ወቅት፣ በሻሂጉቢ ከተማ 15 ሲቪል ሰዎች በህወኃት ኃይሎች ስለመገደላቸው
- በነሐሴ 3/2013 ዓ.ም በመቄት ወረዳ ቀበሌ 15 ደብረ-ዘቢጥ ተብሎ ከሚጠራ ስፍራ አንድ የ7 ዓመት ህጻን ልጅ አንስሳትን ከሚጠብቅበት ቦታ ላይ የትግራይ ኃይል በተተኮሰ በክባድ መሳሪያ ስለመገደሉ
- የትግራይ ኃይል ከነሐሴ 09/2013 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 03/2013 ዓ.ም በደባርቅ ወረዳ፣ የድብባህር ንዑስ ወረዳን ይዘው በቆዩባቸው ግዜያት 5 የአንድ ቤተሰብ ሰዎች የትግራይ ኃይል በተተኮሰ ክባድ መሳሪያ ስለመሞታቸው
- በአጠቃላይ፣ በደባርቅ ወረዳ፣ ድብባህር ንዑስ ወረዳ የትግራይ ኃይል በተተኮሰ ክባድ መሳሪያ 7 ነዋሪዎች ስለመገደላቸው፣ በተጨማሪም በጦርነቱ ምንም ተሳትፎ ያልነበራቸው 4 ነዋሪዎች የትግራይ ኃይል የአካል ጉዳት የደርሶባቸው ስለመሆኑ
- ነሐሴ 12-29/2013 ዓ.ም በደባርቅ፣ በቦዛ ቀጠና የትግራይ ኃይል በተተኮሱ ጥይቶች 38 (ወንድ 31 ሴት 7) ነዋሪዎች የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ስለመሆኑ
- በአብላ ወረዳ ከነሐሴ 14/2013 ጀምሮ በነበረው ጦርነት ከአድከሎ ቀበሌ 12 ሲቪል ሰዎች፣ በጉቢ ቀበሌ 5 ሲቪል ሰዎች እና በወሰማ ቀበሌ 5 ሲቪል ሰዎች በአጠቃላይ 22 ሲቪል ሰዎች በህወኃት ኃይሎች ስለመገደላቸው
- በተመሳሳይ በአድከሎ ቀበሌ 14 ሰዎች፣ በጉቢ ቀበሌ 10 ሲቪል ሰዎች በአጠቃላይ 24 ሲቪል ሰዎች ላይ የትግራይ ኃይሎች የተለያየ መጠን ያለው የአካል ጉዳት ስለመድረሱ
- በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በጭና ቀበሌ የትግራይ ኃይል 26 ነዋሪዎች ላይ በጥይት በመምታት የአካል ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ

- በተሁለደራ ወረዳ 017 ቀበሌ በነበረ ጦርነት 7 ሰዎች የትግራይ ኃይሎች የተገደሉ ስለመሆኑ
- በጳጉሜ 4/2013 ዓ.ም በመቄት ወረዳ፣ በፍላቂት ቀበሌ፣ የትግራይ ኃይሎች በተተኮሰ የክባድ መሳሪያ ጥቃት የአንድ ቤተሰብ አባል የሆኑ 5 ነዋሪዎች እና 2 ጎረቤቶቻቸው በድምሩ የ7 ሰዎች ህይወት ማለፉን እና አብረዋቸው የነበሩ ሌሎች 2 ህጻናት የአካላዊ ጉዳት ስለመድረሱ
- በወረባቡ ወረዳ፣ በቀበሌ 018 ውስጥ በኡርሻ ማሳ ውስጥ ፈንጂ ቀብሮ መተው
- በአፋር ክልል ካሳጊታ፣ በርቃ ከተሞች እና አዋ ወረዳ አለሌ ሱብላ ከተማ አካባቢ በተደረጉ ውጊያዎች የነበረው የክባድ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣
- ከሰሜን ወሎ ዞን ሀብሩ ወረዳ አቅጣጫ ከሚገኝ ተራራማ ቦታ ላይ ወደ ጭፍራ ወረዳ አስኮማ ቀበሌ ቡልቡላ ጃራ(አንዳ ጃራ) መንደር ከተማ የተተኮሱ ክባድ መሳሪያዎች፣

4.3. የትግራይ ኃይሎች ሠላማዊ ሰዎችን እንደ ክለላ በመጠቀም ወይን የሲቪል ተቋማትን ለወታደራዊ አላማ (ለካምፕነት፣ ክባድ መሳሪያ በመጥመድ፣ ምሽግ በመስራት) መጠቀምን በሚመለከት ለአብነትም በሚከተሉት ስፍራዎች የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታ፣ በዚህም ምክኒያት የደረሱ ጉዳቶች ካሉ፣

- በነሐሴ 4/2013 ዓ.ም በመቄት ወረዳ፣ ደብረዘቢጥ ቀበሌ ላይ የትግራይ ተዋጊ ኃይሎች የግለሰብ መኖሪያ ምሽግ አድርገው ሲዋጉ ስለመሆኑ
- የትግራይ ኃይሎች በጳጳት ወረዳን ተቆጣጥረው በነበረበት ወቅት፣በጭና ቀበሌ የጭና ተክለኃይማኖት ቤተክርስቲያንን ምሽግ በማድረጋቸው በጦርነቱ ወቅት ከሁለቱም የጦርነቱ ተሳታፊ አካላት በተተኮሰ ክባድ መሳሪያ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን
- የትግራይ ኃይል ውጊያ በማድረግ ነሐሴ 12-29/2013 ዓ.ም በደባርቅ ወረዳ፣ ቦዛ ቀጠና በሚባሉ የአዲጋግራ፣ የአብርሃም እና የአዲጋት ቀበሌዎችን ይዞ በነበረበት ወቅት የአርሶ አደሮችን መኖሪያ ቤት እንደ ምሽግ መጠቀማቸው
- በአፋር ክልል ካሳጊታ ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን እንደ ካምፕ መጠቀም፣ እና ከትምህርት ቤቱ ጀርባ ታንክ በመጥመድ መታኮስ እና በከተማው በግለሰብ ቤቶች መካከል በመሆን እና ቤቶቹን እንደ ምሽግ በጠቀም፣

4.4. የትግራይ ኃይሎች በተቆጣጠሯቸው አካባቢዎች ተይዘው የተሰወሩ ሲቪል ሰዎችን በሚመለከት የተያዙበት ምክንያት እና አሁን የሚገኙበት ሁኔታ በሚመለከት፣ ለምሳሌ ከአፋር ክልል የቡርቃ ቀበሌ የተወሰዱ 2 ነጋዴዎች፣ አካሳጊታ ከተማ ተይዘው የተወሰዱ ቢያንስ 8 ሰዎች፣

4.5. የትግራይ ታጣቂዎች በህጻናት፣ አዋቂ እና አረጋያን ሴቶች ላይ መፈጸማቸው የተገለጸ በቁጥር በርካታ የአስገድዶ መድፈር ድርጊቶች፣


- በአፋር ክልል ፈንቲ ረሱ ዞን ያሎ ወረዳ ነዋሪ የሆነች ሴት በልጆቿ ፊት የአስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈፀመባት ስለመሆኑ

- በተመሳሳይ በአማራ ክልል ሰሜን ጎንደር ዞን የትግራይ ኃይሎች አካባቢውን ከተቆጣጠሩ በኃላ በየቤቱ በመሄድ የሚያገኙዋቸውን ሴቶች በቤት ውስጥ ወንዶች ካሉ እንዲያወጡ፣ ሴቶቹ ደግሞ ምግብ እንዲሰሩላቸው ካደረጉ እና ከተመገቡ በኃላ ሴቶቹን አስገድደው ወሲባዊ ጥቃት እንደፈፀሙባቸው፣ በደባርቅ ወረዳ ጠዘና፣ አዲ ጋማራ፣ አብርሃም እና አዲጎት ቀበሌዎች የትግራይ ኃይሎች በቆዩባቸው ጊዜያት በሴቶች ላይ ያታዊ ጥቃቶች ስለመፈሰማቸው
- በዚሁ በደባርቅ ወረዳ ድብዛህር ንዑስ ወረዳ የአስገድዶ መድፈር የተፈፀመባት ሴት የትግራይ ኃይሎች 3 ሆነው እንደራ እንድትሰጣቸው ጠይቀው ከበሉ በኃላ ሁለቱ ሲሄዱ አንዱ ወደ እሷ ሲቀርብ ህፃን ነኝ ብትለውም እንኳን ገፍ እንድትል አፏን ይዞ አስገድዶ ከደፈራት በኃላ ወጥቶ መሄዱን የገለፀች ሲሆን፣ በዚሁ ወረዳ አንዲት ሴት በተከታታይ ከኅሐሴ 14 እስከ ቋንሜ 01/ 2013 ዓ.ም ድረስ ለ15 ቀናት በተለያዩ 15 ወንዶች መደፈሯ እንዲሁም በደባርቅ ወረዳ ጭና ቀበሌ አንዲት ሴት ከነሀሴ 26 እስከ ነሀሴ 29 በተከታታይ በተለያዩ ወንዶች መደፈሯን ፣ በተመሳሳይ በጻባት ወረዳ ጭና ቀበሌ ሴት ህፃናት የአስገድዶ መድፈር ጥቃት እንደደረሰባቸው፣
- በተመሳሳይ በደቡብ ጎንደር ዞን ጋዞንት ወረዳ ንፋስ መውጫ የሚገኙ 4 ቀበሌዎች የህወሃት ኃይሎች ወደ ከተማዋ በገቡበት ወቅት የአመራር እና የወታደር ቤት አሳዩን እያሉ በገቡባቸዉ ቤቶች ዉስጥ የተለያዩ ሴቶችን በስለት እና በመሳሪያ በማስፈራራት በተጨማሪም ጥፊ እና መትተት የመሳሰሉ መንገዶችን በመጠቀም ወሲባዊ ጥቃት መፈፀማቸውን
- በሰሜን ወሎ ዞን መቄት ወረዳ ፍላቂት እና ገረገራ ከተማ የተፈፀመ አስገድዶ መድፈር.
- በጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም በኮምቦልቻ ከተማ በሚገኝ አንድ መጠጥ ቤት አምስት የትግራይ ታጣቂዎች ጥይት በመተኮስ አንዲት ሴት እና የ12 ዓመት ልጇን ካቆሰሉ በኃላ በቤቱ ውስጥ የነበሩ አራት ሴቶችን አስገድደው ስለመድፈራቸው፣ በዚሁ ከተማ ጥቅምት 25/2014ዓ.ም ከቀኑ ሰባት ሰአት ላይ አራት የትግራይ ታጣቂዎች አንዲትን ሴት መሳሪያ ደግነው በር እንድትከፍት ካደረጓት በኃላ መሳሪያ ደብቀሻል፣ የብልሶግና ደጋፊነሽ፣ የአብይ ቲሸርት ቤትሽ አለ እንፈትሻለን በማለት ወደ ቤቱ ውስጥ ከገቡ በኃላ አንዱ ታጣቂ በር ላይ ሆኖ ሲጠብቅ የተቀሩት ሁለቱ አስገድደው የደፈሯት ስለመሆኑ፣


4.6. የትግራይ ኃይሎች የደረሱ የንብረት መዝረፍ፣ ማውደም እና ተግባራትን በሚመለከት የነበረው ሁኔታ፣ ይህንን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎች፣ በተጨማሪም በሌሎች ግለሰቦች የመንግስት እና የግለሰብ ንብረቶች ላይ ዝርፊያዎች እንዳይፈፀሙ ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎች፣ ለእብነትም

- የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ 13/2013 ዓ.ም ጀምሮ እዋ ወረዳን የተቆጣጠሩ ሲሆን የሲቪል ሰዎች ንብረት ላይ ዘረፋ የተፈፀመ ስለመሆኑ

- በተመሳሳይ ከሐምሌ 13/2013 ዓ.ም ጀምሮ በአውራ ወረዳ በቆዩበት ወቅት፣ የትግራይ ኃይሎች ብዛት ባላቸው የሲቪል ሰዎች ንብረቶች ላይ የተለያየ መጠንና ዓይነት ያላቸው ጉዳቶች (ማለትም ቃጠሎ፣ዝርፊያ እና አገልግሎት እንዳይሰጡ ማበላሸት) ማድረሱን
- ሐምሌ 16/2013 ዓ.ም የትግራይ ኃይል ወደ አዲ አርቃይ ወረዳ፣ ዛሪማ ንዑስ ወረዳ፣ የበርካታ ሰዎችን ጥሬ ገንዘብ፣ የንግድ መደብሮች እና የመኖሪያ ቤቶችን ከዕለት የምግብ ፍጆታና አልባሳት ጀምሮ እስከ የንግድ እቃዎች እና ሽቀጦች ድረስ የትግራይ ኃይሎች የተዘረፉ መሆኑን
- በደባርቅ ወረዳ በጠዘ በአዲ ጋማራ፣ በአዳጋት እና በአብርሃም ቀበሌዎች የትግራይ ኃይሎች ከኅሐሴ 12 እስከ 29፣ 2013 ዓ.ም ቀበሌዎቹን ተቆጣጥረው በቆዩባቸው ቀናት የቤት እንስሳት (በሬ፣ በግ፣ ፍየል፣ ላም እና ዶሮ) አርደው መብላታቸውን እና የጋማ እንስሳት (አህያ፣ በቅሎ እና ፈረስ) ግማሹን በጥይት መግደላቸውን እና ግማሹን ደግሞ የዘረፋትን ንብረት ጭነው ስለመውሰዳቸው
- የትግራይ ኃይሎች በጻባት ወረዳ፣በጭና ቀበሌ የትግራይ ኃይሎች በደረሱባቸው የግለሰብ ቤት ያገኙትን ንብረት፣ አልባሳትን እና የዕለት የምግብ ፍጆታን ስለመዘረፋቸውና ስለማውደማቸው፣ የቤት እንስሳትን ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል፣ የቀንድ ከብቶችን አርደው በልተዋል፣ በጥይት ስለመግደላቸው፣ እንዲሁም እየተሸነፉ እና ከቀበሌው ሲወጡ የጋማ ከብቶች እንደ አህያ፣ በቅሎ እና ፈረስ ያሉትን ስለመግደላቸው
- የትግራይ ኃይሎች በወራባቡ ወረዳ በቆዩባቸው 7 ቀናት ማለትም ከነሐሴ 24-30/2014 ዓ.ም በአርሻ ማሳዎች ላይ እና በመኖሪያ ቤቶች አካባቢ ፈንጂዎችን ቀብረው እና ጥለው በመሄዳቸው በፍርሃት የመሬት ባለይዞታዎችንና የማሳ ባለቤቶችን ተጨማሪ የልማት ሥራ በመሬቱ ላይ እንዳያከናውኑ ወይም መሬታቸውን ለግብርና ሥራ እንዳይጠቀሙ መሆኑ
- የትግራይ ኃይሎች በተሁለደራ ወረዳ ከነሐሴ 27-29/2013 ዓ.ም በቆዩባቸው ቀናት በወረዳው የሚገኙ 280 የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች ላይ በከባድ መሳሪያ ከፍተኛ እና መክለኛ ወድመት መድረሱን
- ከሐምሌ 08/2013 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ 54 ቀናት ውስጥ በያሉ ወረዳ የሚገኙ 24 የተለያዩ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ መውደማቸውና መዘረፋቸው፣ ለእብነትም በወረዳው የመንግስት ቢሮዎች ውስጥ የሚገኙ ሊጠቅሙ የሚችሉ ቁሳቁሶች (ኮምፒውተሮች፣ ወንበሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ሞተር ሳይክሎች፣ ተሽከርካሪዎች እና የመሳሰሉት) ስለመዘረፋቸው፣ ጠቃሚ እቃዎቻቸውም ተፈተዉ የተወሰዱ ሲሆን የፍርድ ቤትና የፖሊስ መዝገቦችን ጨምሮ የተለያዩ መንግስታዊ ሰነዶች ስለመቃጠላቸውና አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ደረጃ ስለመጎዳታቸው



- በእነዚህ ቀናት ውስጥ በያሉ ወረዳ ጤና ተቋማት ስር (አንድ ጤና ጣቢያና ሶስት ጤና ኬላ) የሚገኙ መድኃኒቶችና ልዩ ልዩ የህክምና ቁሳቁሶች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ስለመዘረፋቸውና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ስለመደረጋቸው
- ከሐምሌ 13/ 2013 ዓ.ም ጀምሮ በአውራ ወረዳ በ17 የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ንብረት ላይ የትግራይ ኃይሎች የተለያየ መጠን እና ዓይነት ያለው ጉዳት ማለትም የቃጠሎ፣ ዝርፊያ እና አገልግሎት እንዳይሰጡ የሚያደርግ ጉዳት ስለመድረሱ፣ ሌላው፣የደራይቱ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የነበሩ የትምህርት መረጃ ቁሳቁሶች ስለመውደማቸው
- በአዲ አርቃይ ወረዳ፣ ዛሪማ ንዑስ ወረዳ የትግራይ ኃይሎች ከሐምሌ 19 እስከ ጳጉሜ 2/20-13 ዓ.ም በነበራቸው ቆይታ፣ የዛሪማ 2ኛ ደረጃ እና 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና የዛሪማ ጤና ጣቢያ የውስጥ ቁሳቁሳቸው (መድሀኒቶች፣ መጽሀፍት፣ የተለያዩ ሰነዶች) መዘረፋቸውን እና መውደማቸውን እንዲሁም መስታወት እና በሮች መሰባበራቸውን፣ በተጨማሪም በእነዚህ ቀናት ውስጥ የትግራይ ኃይሎች በዛሪማ ንዑስ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት፣ ዐ/ህግ ጽ/ቤት፣ ፍ/ቤት፣ መሬ ማዘጋጃ ቤት መዘረፋቸውን እና በውስጥ ቁሰቁሶቻቸው ላይ ውድመት መድረሱን
- የትግራይ ኃይሎች በመቄት ወረዳ ከሐምሌ 24/2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 1/2014 ዓ/ም በነበራቸው ቆይታ በወረዳው የሚገኙ 34 የመንግስት ተቋማት ንብረት ላይ ዘረፋ እና ውድመት የተፈጸመ መሆኑን
- የመቄት ወረዳ ሽሆድ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል በወረዳው የሚገኝ ብቸኛ ሆስፒታል እና ለ270,000 ዜጎች አገልግሎት እየሰጠ የነበረ ሲሆን የትግራይ ኃይሎች ፍላቂት እና ገረገራ ክተሞችን በተቆጣጠሩበት ጊዜያት ማለትም ከሐምሌ 28/2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 10/2014 ዓ.ም በሆስፒታሉ ላይ በርካታ ዘረፋ እና ውድመት መድረሱን
- የመቄት ወረዳ ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ የትግራይ ኃይሎች ከፍተኛ ውድመት የደረሰበት እና የተዘረፈ ተቋም ከመሆኑ በተጨማሪ የትግራይ ኃይሎች የአስክሪን መቅበሪያ ቦታ ስለመደረጉ፣ ኮሌጁ በአርዳታ የተሰጠሱ ከባድ ማሽነሪዎች እና ለግብታ ስራ አገልግሎት የሚውሉ፣ የተግባር ትምህርት የሚሰጥባቸው ቁሳቁሶች ዘረፋ እና ውድመት የደረሰባቸው መሆኑን
- ሌላኛው የትግራይ ኃይሎች ጉዳት የደረሰባቸው ተቋማት የመቄት ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት፣ ትምህርት ጽ/ቤት፣ እና የገረገራ ትምህርት ቤት ሲሆን፣ በገረገራ ትምህርት ቤት አይሲቲ ክፍል ውስጥ የሚገኙ የኮምፒውተር ክፍሎችን በመዝረፍ እና አጋዥ መጽሃፍት አገልግሎት እንዳይሰጡ በዝናብ እንዲበላሹ መደረጉ፣ ከወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት አንድ ደብል ፒኮፕ መኪና፣ ጀነሬተሮች፣ ኮምፒውትሮች፣ ፕላዝማ ቴሌቪዥኖችን ወዘተ ዘረፋ መፈፀሙን
- በተጨማሪም በወረዳው ከሐምሌ 28/2013 ዓ.ም እስከ መስከረም 1/2014 ዓ.ም በነበራቸው ቆይታ በክለዋን ክተማ የሚገኙ የተለያዩ የሀገሪ የወረዳ መንግስታዊ



መስሪያ ቤቶች በሮች እና መስኮቶቻቸው ተሰብረው በውስጥ የነበሩ ቁሳቁሶች ከጥቅም ውጭ መሆናቸው፣የትግራይ ኃይሎች በጉሊና ወረዳ በቆዩበት በክለዋን ክተማና በአካባቢው የሚገኙ የትምህርት እና የጤና ተቋማት አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ደረጃ ስለመውደማቸው

- ለአብነትም፣ የክለዋን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል፣ የጋሊኮማ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ፣ የጋሊኮማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የክለዋን ቴክኒክ እና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ የክለዋን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተዘረፉ ሲሆን፣ የአገልግሎት መስጫ ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች አገለግሎት በማይሰጡበት ደረጃ የተሰባብሩና የተቃጠሉ መሆኑ፣ በተጨማሪም ሉተራናቁሱ ለምች በአርዳታ ለ2500 አባወራዎች የመጣ ምግብ በጋሊኮማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዳለ በቃጠሉ መጎዳቱን
- በተጨማሪም የክለዋን የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታልን የትግራይ ኃይሎች ለወታደራዊ ልምምድ፣ለካምፕነት እንዲሁም ለቆሰሉ ተዋጊዎች የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ይጠቀሙበት እንደነበር እና የሆስፒታሉ ንብረቶች የሆኑ የህክምና አገልግሎት መስጫ መሳሪያዎች (ማይክሮስኮፕ፣የአንስቴዢሪያ ማሽኖች እና አልትራሳውንድ) እና የአምቡላንስ የውስጥ አካላት ተፈተው የትግራይ ሀይሎች እንደተወሰዱ እንዲሁም የሆስፒታል በርና መስኮቶች ተሰብረው መድሃኒቶች፣ የህክምና መገልገያ ማሽኖች፣ መርፌዎች፣ የቀዶ ህክምና ማሽኖች፣የማዋለጃ ቁሳቁሶች፣2 ጀኔሬተሮች፣ ኮምፒተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ፍሪጅ እና ወዘተ ተነቅለውና ተፈታተው መወሰዳቸውን
- እንዲሁም የፌንቲ ረሱ (ዞን 4) ማረሚያ ቤቶች መምሪያ የታራሚዎች ፋይሎች ስለመቃጠሉ፣ የተቋሙ የቢሮ መገልገያ እቃዎች ስለመሰባበራቸው፣ ማረሚያ ቤቱን የትግራይ ኃይሎች ለወታደራዊ አገልግሎት ይጠቀሙበት እንደነበር
- በደባርቅ ወረዳ፣ በቦዛ ቀጠና በአዲ ጋማራ፣ በአዳጋት እና በአብርሃም ቀበሌዎች የትግራይ ኃይሎች ከነሐሴ 12-29/2013 ዓ.ም በቆዩባቸው ቀናት በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት ስለማድረሳቸው፣ የጤና ተቋማትን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ የወረዳ እና የቀበሌ የህዝብ አስተዳደር ተቋማት ቢሮዎችን በስፋት ስለመዝረፋቸው፣ ለመዝረፍ ያልቻሉትን ደግሞ ስለማውደማቸው
- በተጨማሪም የትግራይ ኃይል በደባርቅ ወረዳ፣በድብ ባህር ንዑስ ወረዳ ከነሐሴ 12 እስከ 29/2013 ዓ.ም በቆዩባቸው ጊዜያት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያ፣ ጤና ኤክስቴንሽን ማዕከል፣ ግብርና ማዕከል፣ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ እና ፖሊስ ጣቢያ መዝረፋቸውን እና የቀረውን ንብረት ማውደማቸውን፣ ከነሐሴ 12 እስከ 29/2013 ዓ.ም በቆዩባቸው ጊዜያት የድብ ባህር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በርካታ የክፍሎች በሮችና መስኮቶች ስለማውደማቸው
- የትግራይ ኃይሎች ከነሐሴ 24-29/2013 ዓ.ም በጻባት ወረዳ በቆዩባቸው ቀናት ውስጥ የጭና እና ጻና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ኬላ እና የግብርና ጽ/ቤት የውስጥ ቁሳቁሳቸውን ስለማውደማቸው

- በወረባቡ ወረዳ የትግራይ ኃይሎች ከነሐሴ 24-30/2013 ዓ.ም ድረስ የቆዩ ሲሆን በወረዳው ቀበሌ 018 እና 019 ውስጥ የሚገኙ 4 የመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ የተለያዩ መሣሪያት፣ የሳይንስ ኪቶች፣ የመማሪያ ክፍሎችና የቢሮ በሮች እንዲሁም ጣሪያዎች ላይ የተለያዩ መጠን ያላቸው ጉዳቶች መድረሱ
- በተሁለደራ ወረዳ የትግራይ ኃይሎች ከነሐሴ 27-29/2013 ዓ.ም ድረስ የቆዩ ሲሆን በውረዳው ቀበሌ 017 የሚገኙ 5 የመንግስት ተቋማት እና በቀበሌ 027 የሚገኙ 7 የመንግስት ተቋማት ንብረቶች ላይ ጉዳት እንደደረሰ
- በመቄት ወረዳ 1 ፕራዶ መኪና ንብረትነቱ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን የሰሜን ወሎ ሐገረ-ስብከት ሊቀ-ጳጳስ የሆነ በህወኃት ኃይሎች ስለመወሰዱ
- የትግራይ ኃይሎች በተሁለደራ ወረዳ በነበራቸው የ3 ቀናት ቆይታ በቀበሌ 015 እና 016 የሚገኙ 2 መስጊዶች ላይ እና በቀበሌ 027 የሚገኝ 1 ቤተ-ክርስቲያን ላይ ዘረፋ እና ጉዳት ማድረሳቸውን
- በተመሳሳይ በወረባቦ ወረዳ በነበራቸው የ 7 ቀናት ቆይታ በቀበሌ 018 በ5 መስጊዶች ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ንብረቶች የትግራይ ኃይሎች እንደተወሰዱ እና የህይማኖት መሣሪያት በተለይም ቁርአን እና ኪታቦች እንዲበላሹ እንደተደረገ
- የትግራይ ኃይሎች በአዲ አርቃይ ወረዳ በነበራቸው ቆይታ በዛሪማ ንውስ ወረዳ የንበሬዎች ሁለንብ የህብረት ስራ ማህበር እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዛሪማ ቅርንጫፍ መዘረፋቸውን እና በውስጥ ቁሰቁሶቻቸው ላይ ውድመት መድረሱን
- የትግራይ ኃይል በደባርቅ ወረዳ፣በድብ ባህር ንውስ ወረዳ ከነሐሴ 12 እስከ 29፣ 2013 ዓ.ም በቆዩባቸው ጊዜያት ከሌሎች ጉዳቶች በተጨማሪ የእማራ ብድርና ቁጠባ ተቋምን መዘረፋቸውን እና የቀረውን ንብረት ማውደማቸውን
- በአፋር ክልል ቡርቃ ከተማ ጥቅምት 22 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የተዘረፉ የመንግስት እና የግለሰብ ቤቶች፣ ክረፋዱ ክረፋዱ 5 ሰአት አካባቢ የአንስሳት ህክምና ክሊኒክ፣ የህዝብ ጤና ኬላ እና የአርብቶ አደር ማሰልጠኛ ተሰብረው በውስጥ የነበሩ ንብረቶች እና የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎች ተዘርፈው በመኪና ተጭነው ስለመወሰዳቸው፣
- ጥቅምት 23 ቀን 2014 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎች ካሳጊታን ከተማን ከተቆጣጠሩበት ቀን ጀምሮ በከተማው ጤና ጣቢያ ውስጥ የነበሩ አንድ አልትራ ሳውንድ፣ ሁለት ማይክሮስኮፕ፣ ሁለት ቴሌቪዥን፣ፈራሾች እና አልጋዎች፣አራት ኮምፒውተር፣አንድ ጀኔሬተር፣ መድኃኒቶች እና ሌሎች ንብረቶች እንዲሁም በከተማው የነበሩ አንድ ፋርማሲ መዘረፋቸው፣
- በጥቅምት 08/ 2014 ዓ.ም በጭፍራ ከተማ በሚገኘው ከደቡራ(መስጂደል ራህማ) መስጊድ መስኮት በመስበር እና በመግባት ውስጡ የሚገኙትን የህይማኖታዊ መጽሐፍ(ቁርዓን እና ኪታብ) መቃጠል፣

- ካሳጊታ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የካሳጊታ አንደኛ ደረጃ ትምህርት፣ ጤና ጣቢያ እና አባስ መስጂድ ላይ የደረሱ ንብረት መውደሞች፣
- የትግራይ ኃይሎች በቁጥጥር ስር በነበሩ እና ከሚሸኙ ምርመራ ባደረጓቸው የሸዋ ሮቢት፣ መሐል ሜዳ፣ መሀዙ፣ ሰንበቱ፣ አጣዬ፣ ካራቆሬ፣ አምቦሙሃ መንደር አንጾኪያ ገምካ፣ ከሚሴ፣ መርሶ፣ ውሎሌ፣ ወልዲያ፣ ደሴ፣ ኮምቦልቻ፣ ሐይቅ፣ አርቢት፣ ድብኮ፣ ጋሸና፣ ላሊበላ አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች መፈጸማቸው የተገለጸ እና የተደራጀ መልክ ያላቸው የሚመስሉ የመንግስት አስተዳደር ተቋማት፣ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ሆስፒታሎች፣ ትምርህት ቤቶች ወዘተ)፣ የግለሰቦች የንግድ ተቋማት፣ በመኖሪያ ቤቶች ላይ የተፈጸሙ ዘረፋዎች እና የንብረት ውድመቶች፣

5. ተጠያቂነትን በሚመለከት

- በጦርነት ወቅት የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶችን በሚፈጽሙ አካላት/ታጣቂዎች ላይ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተደራጀ የተጠያቂነት ስርዓት ስለመኖሩ/ያለመኖሩ፣
- የስነ-ምግባር ደንብ ጥሰት ሲከሰት ስለሚወሰድ የተጠያቂነትና የዲሲፕሊን ስርዓት
- በአጠቃላይ ይሁን ከዚህ በላይ በምሳሌነት የተገለጹት ድርጊቶች የትግራይ ኃይሎች አመራሮች እና/ወይም አባላት መፈጸማቸውን የሚያሳይ መረጃ የነበረ ስለመሆኑ፣
- ጥፋቶች በፈጸሙ አባላት ላይ የተከናወነ ምርመራ፣ የተወሰደ የእርምት እርምጃ እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ስራ ስለመኖሩ፣ ከነበረ ዝርዝር መረጃ ቢቀርብ፣
- በቀጣይ ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የተወሰዱ ወይም በመወሰድ ላይ የሚገኙ እርምጃዎች ስለመኖራቸው፣
- እንዲህ ያሉ ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ለአባላት የተሰጠ/በመሰጠት ላይ የሚገኝ ስልጠና/የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ስለመከናወኑ፣

6. ተጨማሪ

- በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ደጋፊ ሰነዶችና ማስረጃዎች ካሉ፣
- ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች እና ማብራሪያዎች

አባሪ 4

ከኢሰመኮ ለኢ.ፌ.ድ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ



በኢ.ፌ.ዴ.ሪ
የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር [redacted]

ጉዳዩ፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመጠየቅ፤


የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ክትትል እና ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅ/ቤት ጋር በጋራ በመሆን የፌደራል መንግስት ኃይሎች ከትግራይ ክልል አስከወጡበት ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳዮች ላይ ምርመራ በማድረግ የጋራ ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

ኮሚሽኑ ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ የተፈፀሙና በተለይም ግጭቱ ቀጥሎ በተስፋፋባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ለማካሄድ በተለያዩ ጊዜያት የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት ምርመራ አድርጓል።

ኮሚሽኑ ያከናወነው ምርመራ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ዘዴዎችን በመከተል ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በገለልተኝነት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። የምርመራው ዘዴም በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉም አካላት ተፈፀሙ በተባሉት ጥሰቶች ላይ ምላሽ እና ማስረጃ እንዲሰጡ ማድረግን ይጨምራል።

ስለሆነም በተደረገው ምርመራ መሰረት የተለዩትን ሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎችና አጠቃላይ የነገሩን ሁኔታ በሚመለከት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን በዚህ ደብዳቤ አባሪነት የላክን መሆኑን እየገለፅን፤ የአናንተን ምለሽ እና አስተያት በሪፖርታችን ለማካተት ይቻል ዘንድ ምላሻችሁን ይህ ደብዳቤ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 የስራ ቀናት ውስጥ እንድትልኩልን በማክበር እንጠይቃለን።

ሰብአዊ መብቶች የማይገሰሱ፣ የማይሸራረፉ እና ሁሉ አቀፍ መብቶች ናቸው።
Human Rights are Inalienable, Indivisible and Universal Rights



ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በኢሜል yibekal.gizaw@ehrc.org ስ.ቁ ፡- 09 11 81 70 02 ወይምኢሜል manyawkal.mekonnen@ehrc.org ስ.ቁ ፡-09 11 62 11 23 ኢሜል mesganaw.mulugeta@ehrc.org ስ.ቁ:- 09 11 10 57 71 ማነጋገር ይቻላል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

[redacted]

ለሀገር መከላከያ ሚኒስቴር /ለኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት የተዘጋጀ የጥያቄ መዘርዝር

1. **አጠቃላይ**

- የመከላከያ ሰራዊቱ መዋቅርና የኮማንድ ፖስት አደረጃጀት ሁኔታ፣ መከላከያ ከክልል ልዩ ኃይሎች፣ ሚሊሻና ፋኖ ጋር ያለው ግንኙነትና የአዝ ሰንሰለት ምን ይመስላል?
- በአማራና አፋር ክልሎች በተካሄዱ ውጊያዎች የክልሎች የፀጥታ ኃይሎች (የአፋር፣ አማራ፣ የሌሎች ክልሎች ልዩ ኃይሎች፣ ፖሊሶች፣ ሚሊሻዎች እና ሌሎች የወጣቶች አደረጃጀቶች) መቼና በየትኞቹ ቦታዎች ተሳተፉ?
- የመከላከያ ሰራዊት እና አጋር ኃይሎች በአማራ ክልል እና በአፋር ክልል የሚገኙ ዞኖች እና ወረዳዎችን ከትግራይ ኃይሎች መልሰው የተቆጣጠሩበት ጊዜ (date of effective control) (በወረዳ ወይም ከተማ ደረጃ ሊገለጽ ይችላል)

2. **ዝግጁነት፣ ስነምግባር ደንብ እና አያያዝ**

- ሰራዊቱና አመራሩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግን ለመተግበር ስላለው ዝግጁነት፣ የወሰዱት ስልጠና እና የተሻሬ የስነ-ምግባር ደንብ ስለመኖሩ?
- ከስምሪታቸው በፊት ለሲቪሎች ስለሚደረግ ጥበቃ፣ ጥንቃቄ ስለመውሰድና ስለተመጠጠኝነት ወሰዱት ስልጠና እና ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?
- የተማረኩ የትግራይ ታጣቂዎች ብዛት እና የአያያዝ ሁኔታ፣ የህክምና አርዳታን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶች ሁኔታ?

3. **የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች**

መከላከያ ሰራዊት ወይም በመከላከያ ሰራዊት ቁጥጥር ስር የሰብአዊ መብቶች እና ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ተፈፅሞባቸዋል ተብለው በተለዩት የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ እና ማስረጃዎች እንዲቀርቡ፣

3.1. የመከላከያ ሰራዊት በትግራይ ክልል ባደረጋቸው የአየር እና የድሮን ጥቃቶች ወቅት በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚወስደው አጠቃላይ እርምጃ እና በተለይም ከዚህ በታች በተረዘሩት ክስተቶች ወቅት የነበረው የወታደራዊ ኢላማ እና በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት ላለማድረስ እና ሲቪል ሰዎችን ለመለየት የተደረጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች በሚመለከት ማብራሪያ፣

- ሰኔ 15 ቀን 2013 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 7:00 ሰዓት በትግራይ ክልል ደቡብ ምስራቅ ዞን እንደርታ ወረዳ ደብረናዝሬት ጣብያ ቶጎን ጎጥ በሚገኘው የመገበያያ ቦታ፣
- ጥቅምት 08 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰአት መቐሌ ከተማ መሶቦ አካባቢ እና ከምሽቱ 12:30 ላይ መቐሌ ከተማ ሀውልቲ ክፍለ ከተማ ፕላኔት ሆቴል፣
- ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም መቐሌ ከተማ መስፍን ኢንዳስትርያል ኢንጅነሪንግ፣
- ጥቅምት 13 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 10:00 አካባቢ በመቐሌ ከተማ ሰሜን ክፍለ ከተማ ላፈ በሚባል አከባቢ ባለው የከተማው መብራት ሃይል ሳብ ስቴሽን፣
- ጥቅምት 18 ቀን 2014 ዓ.ም ከቀኑ 5:00 በመቐሌ ከተማ ሰሜን ክፍለ ከተማ 06 ቀበሌ ደረቅ ወደብ በሚባል አከባቢ በሚገኙት የግል መኖሪያ ቤቶች

3.2. የመከላከያ ሰራዊት ከትግራይ ኃይሎች ጋር በተሰያዩ የአማራ እና አፋር ክልል አከባቢዎች ባደረጋቸው ውጊያዎች የነበሩ የከባድ መሳሪያ አጠቃቀምን በሚመለከት በጦርነት ሂደት ወታደራዊ ዓላማ ጥቃት በሚፈጸምበት አከባቢ መኖሩን የማረጋገጥ፣ የተመጣጣኝነት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰዳቸውን በማያሳይ አግባብ በተፈጸሙ የከባድ መሳሪያ ጥቃቶች፣ የድሮን እና የጀት ድብደባዎች ምክንያት የሞቱ እና ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲቪል ሰዎች መኖራቸው፣ በተሰይም ከዚህ በታች በተረዘሩት ስፍራዎች እና ክስተቶች ወቅት የነበረው የወታደራዊ ኢላማ እና በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት ላለማድረስ እና ሲቪል ሰዎችን ለመለየት የተደረጉትን የጥንቃቄ እርምጃዎች በሚመለከት ማብራሪያ፣ በጥቃቶቹም የደረሱት ተጓዳኝ ጉዳቶች ቢዘረዘሩ፣

- በአማራ ክልል በነሐሴ 4/2013 ዓ.ም በመቄት ወረዳ፣ ደብረዘቢጥ ቀበሌ ላይ ከመከላከያ ኃይሎች በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ በአንድ ግለሰብ መኖሪያ ቤት ላይ ጉዳት ስለመድረሱ
- በነሐሴ 12-29/2013 ዓ.ም በደባርቅ ወረዳ፣ ቦዛ ቀጠና በሚባሉ የአዲጋራ፣ የአብርሃም እና የአዳጋት ቀበሌዎችን ይዞ በነበረበት ወቅት በመከላከያ ሰራዊት አባላት ወደ አርሶ አደሮች ቤት ከባድ መሳሪያ በመተኮሳቸው 6 ሰዎች መገደላቸው
- በነሐሴ 25/2013 ዓ.ም በደበርዘቢጥ ቀበሌ ከመከላከያ ኃይሎች በኩል በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ የአንድ አርሶ አደር ግቢ ውስጥ በመውደቁ የ1 ሰው ህይወት ማለፉ
- በነሐሴ 29/2013 ዓ.ም ከቀኑ 6:00 አካባቢ ከመከላከያ ሰራዊት የተተኮሰ ከባድ መሳሪያ በመቄት ወረዳ፣ ፍላቂት ቀበሌ ስዩም መታሰቢያ ሆቴል አከባቢ የ7 ነዋሪዎች ህይወት ማለፉ እና 1 ነዋሪ ላይ ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱ

- ኑሐሴ 26/2013 ዓ.ም በወረባቦ ወረዳ፣ቀበሌ 018 በነበረ ውጊያ የቀበሌው ነዋሪ በመኖሪያ ቤቷ ውስጥ እያለች ከመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ፍንጣሪ ተመታ ህይወቷ ማለፉ

- ከነሐሴ 27-29/2013 ዓ.ም ተሁለደሬ ወረዳ በነበረ ጦርነት 8 ነዋሪዎች ሲሞቱ 6ቱ ከመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ተመተው ህይወታቸው ማለፉ

- በተሁለደሬ ወረዳ 017 ቀበሌ በነበረ ጦርነት ህይወታቸው ካለፈ ሰዎች መካከል 6 ሰዎች ከመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያዎች ተመተው ህይወታቸው ማለፉ

- በተሁለደሬ ወረዳ፣ የቀበሌ 017 ነዋሪ የሆኑ 4 ነዋሪዎች ከአንድ ቤተሰብ በነሐሴ 29/2013 ዓ.ም በነበረ ጦርነት ከመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ ተመተው ህይወታቸው ማለፉ

- በነሐሴ 29/2013 ዓ.ም በነበረ ጦርነት በመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ጥይት 1 ግለሰብ ላይ የአካል ጉዳት መድረሱ

- በነሐሴ 30/2013 ዓ.ም. በደብረዘቢጥ ቀበሌ ከመከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ ከባድ መሳሪያ የ13 ዓመት ታዳጊ ልጅ ህይወት ማለፉን እና ሌሎች 3 ሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት መድረሱ

- በደባርቅ ወረዳ፣በድብ ባህር ንዑስ ወረዳ በጤና ጣቢያ እና በሌሎች ተቋማትን መከላከያ ሠራዊት እንደ መጠለያ መጠቀሙ

- አለሌ ሱብላ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አከባቢ ይገኝ የነበረው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወደ አማራ ክልል ሰሜን ወሎ ዞን ድራ ሮቃ ወረዳ አቅጣጫ የተኮሳቸው ከባድ መሳሪያዎች፣

- በሸዋ ሮቢት ከተማ ከሀገር መከላከያ ሰራዊት በተተኮሰ የከባድ መሳሪያ ጥይት እና ድሮን ጥቃት 7 ሲቪል ሰዎች የተገደሉ መሆኑን፤ ታህሣሥ 9 ቀን 2014ዓ/ም ከቀኑ በግምት 9:00 ሰዓት ሲሆን ወልዲያ ከተማ ቀበሌ 02 በተለምዶ ፒያሳ በተባለው አካባቢ ከአንድ ሆቴል አጠገብ የድሮን ጥቃት ተፈጽሞ በሀንፃው በረንዳ ላይ የነበሩ በጦርነቱ ምንም ዓይነት ተሳትፎ የሌላቸው 6 ሲቪል ሰዎች ላይ የሞት አደጋ የደረሰ ሲሆን 4 ሰዎች ላይ ደግሞ የመቁሰል አደጋ መድረሱ፤

3.3. የመከላከያ ሰራዊት ሲቪል ተቋማትን ለወታደራዊ አላማ (ለካምፕነት፣ ከባድ መሳሪያ በመጥመድ፣ ምሽግ በመስራት) መጠቀምን በሚመለከት ለአብነትም በሚከተሉት ስፍራዎች የነበረውን አጠቃላይ ሁኔታ፣ በዚህም ምክኒያት የደረሱ ጉዳቶች ካሉ፤

ለአብነትም በእዋ ወረዳ አለሌ ሱብላ ከተማ ወጣ ብሎ የሚገኘውን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለወታደራዊ አግልግሎት መጠቀም፣

3.4. የትግራይ ወይም የአነግ ሸኔ ታጣቂ ኃይሎች አባላት ናችሁ ወይም አብራችኋል በሚል ግድያ የተፈጸመባቸው ሲቪል ሰዎች ስለመኖራቸው፤ ለምሳሌም ምስክሮች ቀኑን በውል ባልለዩት የታህሳስ ወር 2014 መጀመሪያ ሳምንት ለጊዜው ማንነታቸው ያልታወቁ በግምት 30 የሚሆኑ የሲቪል ልብስ የለበሱ ሰዎች በመከላከያ ሰራዊት አባላት በኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ደዋ ጨፋ አካባቢ እንዲመጡ ከተደረገ በኃላ ለሶስት ቀናት ድብደባ እና የማሰቃየት ተግባር ሲፈጸምባቸው ቆይቶ በጅምላ ተረሽነው ጉድጓድ ውስጥ እንዲጣሉ ስለመደረጉ፤ በሰንበቴ ከተማ "የሸኔ አባል ናችሁ" በሚል ከመኖሪያ ቤታቸው በመከላከያ ሰራዊት አባላት ከተወሰዱ በኃላ በጥይት ተደብድበው ተገድለው የተገኙ አራት ነዋሪዎች ስለመኖራቸው፤

3.5. በግጭቱ አካባቢዎች ተከሰተው ስለነበሩ የሰብአዊ እርዳታ ማጓጓዝ ክልከላዎችና ገደቦች ለአብነትም ወደ ትግራይ ክልል የሚሄዱ የእርዳታ መኪኖች መከልከል እና በትግራይ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በነበሩ ስፍራዎች የእርዳታ አቅርቦት ስለመከልከሉ

4. ተጠያቂነትን በሚመለከት

- በጦርነት ወቅት የሰብአዊ መብቶች እና የሰብዓዊነት ሕግ ጥሰቶችን በሚፈጽሙ አባላት/ታጣቂዎች ላይ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል የተደራጀ የተጠያቂነት ስርዓት ስለመኖሩ/ያለመኖሩ፤
- የስነ-ምግባር ደንብ ጥሰት ሲከሰት ስለሚወሰድ የተጠያቂነትና የዲሲፕሊን ስርዓት
- በአጠቃላይ ይሁን ከዚህ በላይ በምሳሌነት የተገለጹት ድርጊቶች በመከላከያ ሰራዊት አመራሮች እና/ወይም አባላት መፈጸማቸውን የሚያሳይ መረጃ የነበረ ስለመሆኑ፤
- ጥፋቶች በፈጸሙ አባላት ላይ የተከናወነ ምርመራ፣ የተወሰደ የእርምት እርምጃ እና ተጠያቂነትን የማረጋገጥ ስራ ስለመኖሩ፣ ከነበረ ዝርዝር መረጃ ቢቀርብ፤
- በቀጣይ ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች እና የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የተወሰዱ ወይም በመወሰድ ላይ የሚገኙ እርምጃዎች ስለመኖራቸው፤
- እንዲህ ያሉ ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ለአባላት የተሰጠ/በመሰጠት ላይ የሚገኝ ስልጠና/የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ስለመከናወኑ፤

5. ተጨማሪ

- በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ደጋፊ ሰነዶችና ማስረጃዎች ካሉ፣
- ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች እና ማብራሪያዎች

አባሪ 5

ከኢሰመኮ ለትምህርት ሚኒስቴር የተላከ ደብዳቤ




ቁጥር፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመጠየቅ!

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ክትትል እና ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ዕቤት ጋር በጋራ በመሆን የፌደራል መንግስት ኃይሎች ከትግራይ ክልል አስከወጡበት ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳዮች ላይ ምርመራ በማድረግ የጋራ ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።


ኮሚሽኑ ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ የተፈፀሙና በተለይም ግጭቱ ቀጥሎ በተስፋፋባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ለማካሄድ በተለያዩ ጊዜያት የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት ምርመራ አድርጓል።

ኮሚሽኑ ያከናወነው ምርመራ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ዘዴዎችን በመከተል ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በገለልተኝነት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። የምርመራው ዘዴም በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉም አካላት ተፈፀሙ በተባሉት ጥሰቶች ላይ ምላሽ እና ማስረጃ እንዲሰጡ ማድረግን ይጨምራል።

ስለሆነም በተደረገው ምርመራ መሰረት የተለዩትን ሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎችና አጠቃላይ የነገሩን ሁኔታ በሚመለከት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን በዚህ ደብዳቤ አባሪነት የላክን መሆኑን እየገለፅን፣ የእናንተን ምላሽ እና አስተያየት በሪፖርታችን ለማካተት ይቻል ዘንድ ምላሻችሁን ይህ ደብዳቤ ከተላፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 የስራ ቀናት ውስጥ እንድትልኩልን በማክበር እንጠይቃለን።



ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በኢሜል yibekal.gizaw@ehrc.org ስ.ቁ ፡- 09 11 81 70 02 ወይምኢሜል manyawkal.mekonnen@ehrc.org ስ.ቁ ፡-09 11 62 11 23 ኢሜል mesganaw.mulugeta@ehrc.org ስ.ቁ:- 09 11 10 57 71 ማነጋገር ይቻላል።



ለትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀ የጥያቄ መዘርዝር

አጠቃላይ

- በአማራና አፋር ክልሎች የግጭት አካባቢዎች የትምህርት ተቋማትና የትምህርት አገልግሎት አቅርቦት ሁኔታ
- በግጭቱ አካባቢዎች በትምህርት ተቋማት ላይ ስለደረሰ ዝርፊያ እና ውድመት ይህንን ለማጣራት ስለተወሰደ እርምጃ
- በግጭቱ አካባቢዎች ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት በሚኒስቴሩ የተደረገ ድጋፍ

ዝርዝር ኩነቶችና በትምህርት ተቋማት ላይ የደረሰ ጉዳት

- በአፋር ክልል በጋሊኮማ ቀበሌ፤ በአውራ ወረዳ በደራይቱ ከተማ
- በአማራ ክልል የመቄት ወረዳ በዛሪማ ከተማ፤ በድብ ባህር
- በወረባቡ ወረዳ የትምህርት ተቋማት ላይ የደረሰ ዝርፊያ እና ውድመት

አባሪ 6

ከኢሰመኮ ለፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የተላከ ደብዳቤ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
Federal Democratic Republic of Ethiopia

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

ቁጥር ሰመኮ/ፌ.ሪ/ደ/ስ/ክ/2014
Ref. No.
ቀን 21 ጥር 2014
Date
ስልክ Tel.
ፋክስ Fax
ፖ.ሣ.ቁ.ር P.O.Box 1185
ኢ-ሜይል E-mail hrcom@ethionet.et
አዲስ አበባ
Addis Ababa

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ

የፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን [redacted]

ጉዳዩ፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመጠየቅ፤


የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ሕሊዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ለሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፤ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ክትትል እና ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል። በተለይም ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅ/ቤት ጋር በጋራ በመሆን የፌደራል መንግስት ኃይሎች ከትግራይ ክልል እስከወጡበት ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳዮች ላይ ምርመራ በማድረግ የጋራ ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

ኮሚሽኑ ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ የተፈፀሙና በተለይም ግጭቱ ቀጥሎ በተስፋፋባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ለማካሄድ በተለያዩ ጊዜያት የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት ምርመራ አድርጓል።

ኮሚሽኑ ያከናወነው ምርመራ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ዘዴዎችን በመከተል ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በገለልተኝነት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። የምርመራው ዘዴም በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉም አካላት ተፈፀሙ በተባሉት ጥሰቶች ላይ ምላሽ እና ማስረጃ እንዲሰጡ ማድረግን ይጨምራል።

ስለሆነም በተደረገው ምርመራ መሰረት የተለዩትን ሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎችና አጠቃላይ የነገሩን ሁኔታ በሚመለከት ኮሚሽኑ ምላሽ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን በዚህ ደብዳቤ አባሪነት የላክን መሆኑን እየገለፅን፤ የእናንተን ምላሽ እና አስተያየት በሪፖርታችን ለማካተት ይቻል ዘንድ ምላሻችሁን ይህ ደብዳቤ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 የስራ ቀናት ውስጥ እንድትልኩልን በማክበር እንጠይቃለን።

ሰብአዊ መብቶች የማይገሠሡ፣ የማይሸራረፉ እና ሁሉም [illegible]
Human Rights are Inalienable, Indivisible and Universal Rights




ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በኢሜል yibekal.gizaw@ehrc.org ስ.ቁ ፡- 09 11 81 70 02 ወይም ኢሜል manyawkal.mekonnen@ehrc.org ስ.ቁ ፡-09 11 62 11 23 ኢሜል mesganaw.mulugeta@ehrc.org ስ.ቁ፡- 09 11 10 57 71 ማነጋገር ይቻላል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

[redacted]

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን
ዋና ኮሚሽነር



ለፌዴራል አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን (ለሁለቱ ክልሎች አደጋ ስጋት ስራ አመራር ቢሮዎች) የተዘጋጀ የጥያቄ መዘርዝር

አጠቃላይ

- በግጭቱ አካባቢዎች ስላለው የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነትና የሰብአዊነት ሁኔታ፤ የምግብ ዋስትና
- በአማራና አፋር ክልሎች በተካሄዱ ውጊያዎች የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ብዛትና ሁኔታ፤ የሚገኙበት ቦታ፤ ለተፈናቀሉ ነዋሪዎች ስለተደረገ ሰብአዊ ድጋፍ
- በግጭቱ አካባቢዎች ስላለው የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነት፤ገደቦችና ክልከላዎች

ስለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች

- በግጭቱ አካባቢዎች ስለሚገኙ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሁኔታና ተፈናቃዮችን ወደመኖርያቸው ለመመለስ እና ለማቋቋም ስለተከናወኑ ተግባራት
- በቂ የሰብአዊ ድጋፍ አለመቅረብና የእርዳታ ተደራሽነት ላይ የተጣሉ ገደቦችን በሚመለከት የተደረገ ማጣራትና የተወሰደ እርምጃ

አባሪ 7

ከኢሰመኮ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተላከ ደብዳቤ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
Federal Democratic Republic of Ethiopia
የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

ቀን 21/05/2014

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ
የብሔራዊ ባንክ
[redacted]

ጉዳዩ፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመጠየቅ!


የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) በፌደራል ሕገ መንግስቱ መሰረት ነጻ ፌደራላዊ መንግስት አካል ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 210/1992 (በአዋጅ ቁጥር 1224/2012 እንደተሻሻለው) የተቋቋመና ሰሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆነ ሰሰብአዊ መብቶች መስፋፋት፣ መከበርና እና ጥበቃ የሚሰራ ብሔራዊ የሰብአዊ መብቶች ተቋም ነው። ኮሚሽኑ በትግራይ ክልል ግጭት ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ክትትል እና ምርመራ ሲያደርግ ቆይቷል። በተሰይም ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽነር ፅቤት ጋር በጋራ በመሆን የፌደራል መንግስት ኃይሎች ከትግራይ ክልል አስከወጡበት ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ የተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰት ጉዳዮች ላይ ምርመራ በማድረግ የጋራ ሪፖርቱን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

ኮሚሽኑ ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ የተፈፀሙና በተሰይም ግጭቱ ቀጥሎ በተስፋፋባቸው የአማራ እና የአፋር ክልል አካባቢዎች የተከሰቱ የሰብአዊ መብቶች እና የዓለም አቀፍ ሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ለማካሄድ በተሰያዩ ጊዜያት የምርመራ ቡድኖችን በማሰማራት ምርመራ አድርጓል።

ኮሚሽኑ ያከናወነው ምርመራ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ምርመራ ዘዴዎችን በመከተል ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በገለልተኝነት መርህ ላይ የተመሰረተ ነው።፤ የምርመራው ዘዴም በግጭቱ የተሳተፉ ሁሉም አካላት ተፈፀሙ በተባሉት ጥሰቶች ላይ ምላሽ እና ማብራሪያ እንዲሰጡ ማድረግን ይጨምራል።


ስለሆነም በተደረገው ምርመራ መሰረት የተሰዩትን ሰብአዊ መብቶች እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥሰቶች የሚመለከቱ ጥያቄዎችና አጠቃሰይ የነገሩን ሁኔታ በሚመለከት ባንኩ ምላሽ እንዲሰጥባቸው የሚያስፈልጉ ጥያቄዎችን በዚህ ደብዳቤ አባሪነት የሳክን መሆኑን እየገለፅን፣ የእናንተን ምላሽ እና አስተያየት በሪፖርታችን ለማካተት ይቻል ዘንድ ምላሻችሁን ይህ ደብዳቤ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 7 የስራ ቀናት ውስጥ እንድትልኩልን በማክበር እንጠይቃለን።

ሰብአዊ መብቶች የማይገሠሡ፣ የማይሸራረፉ እና ሁሉ አቀፍ ናቸው።
Human Rights are Inalienable, Indivisible and Universal



ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ በኢሜል yibekal.gizaw@ehrc.org ስ.ቁ ፡- 09 11 81 70 02 ወይምኢሜል manyawkal.mekonnen@ehrc.org ስ.ቁ ፡-09 11 62 11 23 ኢሜል mesganaw.mulugeta@ehrc.org ስ.ቁ:- 09 11 10 57 71 ማነጋገር ይቻላል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር
[redacted]




ለብሔራዊ ባንክ

በአማራና አፋር ክልሎች በግጭቱ አካባቢዎች የትግራይ ኃይሎች በባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ላይ የደረሰው ዝርፊያና ውድመት ምን ይመስላል?

የተጎዱ ባንኮችና የፋይናንስ ተቋማት ዝርዝር ድርጊቱ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፤በብሔራዊ ባንክ የተደረገ ማጣራትና ድጋፍ

አባሪ 8

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. መከላከያ ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ



ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመስጠት


የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተደረጉ ጦርነቶች ላይ በተሰይ ደግሞ ከሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ/ም በኋላ በአፋር እና በአማራ ክልል ተፈፅመዋል በተባሉ የሰብአዊነት ህግ ጥሰቶች ላይ ምርመራ ማድረጉን በመግለፅ በተሰያዩ ቦታዎች በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወገን ተፈፅመዋል ያላቸውን የሰብዓዊነት መብት ጥሰቶች በመለየት መከላከያ ሚኒስቴር በቀረቡት መዘርዝር ጥያቄዎች ላይ በሰባት(7)ቀን ውስጥ አስፈላጊውን ማስረጃ እና ምላሽ እንዲሰጥበት በተጠየቀው መሰረት እንደሚከተለው አቅርቦናል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የምርመራ ውጤት በደብዳቤ ለመከላከያ ሚኒስቴር የደረሰው የተቀመጠው ቀን ገደብ ካለፈ በኋላ ከመሆኑ ባሻገር በአባሪው የቀረበው የምርመራ ውጤት ይዘቱ ሰፊ እና በቁጥር ሰፋ ያለ ከመሆኑ አኳያ ምላሽ በሚፈልጉ አያንዳንዱ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊውን ምላሽ ለመስጠት ሰፊ ጊዜ እና ትኩረት የሚጠይቅ እንደመሆኑ የመከላከያ ወታደራዊ አቃቢ ህግ ዋና ዳይሬክቶሬት ክፍፍር የመከላከያ ሚኒስትሩ የተሰጠውን ትዕዛዝ መሰረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ስራዎችን በመስራት ላይ ነው።

ይሁን እንጅ በኮሚሽኑ ምላሽ ከተጠየቀባቸው ጉዳዮች መካከል ከፊሉ ከሚመለከታቸው የጦር ክፍሎች ማስረጃ ማሰባሰብ የሚጠይቁ፣ የተወሰኑት ደግሞ ምርመራ ማድረግን የሚፈልጉ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ጉዳዮች ደግሞ አሁንኑ ምላሽ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ናቸው።


ስለሆነም፡-

1. ከመከላከያ ሰራዊት መዋቅር እና አደረጃጀት፣ ከክልል ልዩ ሃይሎች ጋር ያለውን ትስስር እና የፅዘ ሰንሰለት በሚመለከት ማብራሪያ እንዲሰጥ ጥያቄ ቀርቧል። የኢፌዲሪ መከላከያ የሚታወቅ በህግ የተደነገገ ግልፅ እና ዘመናዊ የሆነ አደረጃጀት ያለው ሲሆን በዋናነት በመከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀፅ 4 ድንጋጌ መሰረት በሃይሎች(አየር ሃይል፣ ምድር ሃይል፣ ባህር ሃይል፣ የልዩ ዘመቻዎች ሃይል እና በስፔስ እና ሳይበር ሃይል) የተደራጀ ሲሆን እነዚህ ሃይሎች እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ተቋማዊ ህጎች መሰረት በዕዝ፣ በክፍለጦር፣ በብርጌድ እና በሻለቃ የተዋቀሩ ናቸው።
ይህ መዋቅር በተደራጀ የፅዘ ሰንሰለት የሚመራ ሲሆን በመከላከያ ሰራዊት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 460/2012 አንቀፅ 20 ድንጋጌ መሰረት



ወታደራዊ አዛዦችን ለመሾም ስልጣን በተሰጣቸው አካላት መሰረት በሚሰጥ ሹመት የሚመሩ ናቸው።

2. ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር ሰራዊቱ ያለውን ግንኙነት በሚመለከት የመከላከያ ሰራዊቱ ከክልል እና ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር የሚያገናኘው ምንም አይነት የአደረጃጀትም ይሁን የፅዘ ሰንሰለት የለውም።
3. ከአለማቀፍ የጦርነት ህግጋቶች ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በአግባቡ የሰለጠነ ግጻጼን በውል የሚረዳ ፕሮፌሽናል ሰራዊት ሲሆን የትኛውንም ወታደራዊ ግጻጼ ሲፈፅም ተልዕኮውን በውል እንዲገነዘብ፣ የሃይል አጠቃቀሙም አለማቀፍ የጦርነትን ህግን የተከተለ እንዲሆን አስፈላጊውን ስልጠና ቀድሞ እንዲወስድ ተደርጓል።
በዚህ ረገድ ተቋሙ በቂ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ያለው ሲሆን በመከላከያ ሰራዊት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 460/2012 አንቀፅ 8(17) እና 8(18) ድንጋጌዎች ላይ እንደትደም ተከተላቸው ከምርኮኛ አያያዝ እና በአለማቀፍ ህግ አንዳይጠቁ ከለላ ያላቸውን አካላት የመጠበቅ ግዴታ በማንኛውም የሰራዊት አባል ላይ በደንቡ ግዴታ ተጥሏል።
መከላከያ ሰራዊቱ አጠቃላይ ወታደራዊ ግጻጼን ሲፈፅም የሃይል አጠቃቀሙን፣ የጥንቃቄ አርምጃ አወሳሰዱን እና አጠቃላይ በጦርነት ወቅት አሰማቀፍ የጦርነት ህጎችን አንዱት ማክበር አንዳለበት በገርገር የሚደነግግ ቋሚ የግጻጼ አፈፃፀም ደንብ(standing rule of engagement) ያለው ከመሆኑ ባሻገር በእያንዳንዱ ግጻጼ የጦርነቱን አጠቃላይ ሁኔታ እና የጠላትን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ የግጻጼ አፈፃፀም የኪስ ካርድ ተዘጋጅቶ ለሁሉም የሰራዊት አባል የተሰጠ ሲሆን መከላከያ በአፋር እና በአማራ ክልል አሸባሪውን ሃይል ለመከላከል ባደረጋቸው ጦርነቶች አነዚህ የኪስ ካርዶች ተዘጋጅተው ለሰራዊቱ አና ለሁሉም የፀጥታ አካላት ተሰጥተዋል።
አለማቀፍ የጦርነት ህጎችን በሚመለከት ሁሉም የመከላከያ ሰራዊት አባላት ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል ለምሳሌ አንድ ፅጫ (ምልምል) ወታደር በማሰልጠኛ ተቋማት ከሚወሰደው ወታደራዊ ስልጠና በተጨማሪ በጦርነት ህጎች ላይ ትምህርት እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን በየደረጃው ላሉ አዛዦችም ከአለማቀፍ የቀይ መስቀል ማህበር ጋር በመተባበር ስልጠና ተሰጥቷል። አጠቃላይ ከግጻጼ ስምሪት ጎን ለጎን ለ72,260 (ሰባ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ) ለሚሆኑ በየደረጃው ለሚገኙ የሰራዊት አዛዦች ተደጋጋሚ ስልጠና ተሰጥቷል።
ይህ ስልጠና አሁንም ከክፍተኛ ወታደራዊ የህግ ሙያተኞች እና ከአለማቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ጋር በመተባበር በመሰጠት ላይ ይገኛል።
4. በቀረቡት አያንዳንዱ ጉዳዮች ላይ አስፈላጊውን ምርመራ በማድረግ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በከሚሽኑ የምርመራ ውጤት መሰረት የመከላከያ ሰራዊት የህጠሳት አሸባሪ ቡድን የአማራ እና የአፋር ክልልን ጥሶ በመግባት በሰው እና በንብረት ላይ ያደርስ የነበረውን ጉዳት ለመከላከል በተደረጉ ጦርነቶች ሰራዊቱ በጠላት ላይ ወታደራዊ አርምጃ ሲወስድ በተሰይ ደግሞ የክፍ መሰረያ ድብደባዎች፣ የአየር እና የድሮን ጥቃቶች በተሰያዩ የአማራ እና የአፋር ክልል ቦታዎች በተሰያዩ



ውጤቶች በሰዎች ላይ የሞት እና የአካል መጉደል እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት ስለመድረሱ የሚገልፅ ነው።

በዚህ ረገድ በየትኛውም ጦርነት ተጓዳኝ ጉዳቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚገመት ቢሆንም በተለይ ደግሞ የአሸባሪው ቡድን ከሚከተሰው የማሞቡርበር የጦርነት ስልት አኳያ ተጓዳኝ ጉዳቶች ከፍ ማለታቸው የማይቀር ነው። ጠላት የሲቪል መገልገያ ተቋማትን ለወታደራዊ አላማ ይጠቀም የነበረ ሲሆን የጠላት ተዋጊዎችም የማሰሰብ መኖሪያ ቤቶችንም ላይቀር ለጦርነት ጥቅም አውሏል።

በመሆኑም በክባድ መሳሪያ ተኩስ ወቅት ጠላትን ኢላማ ያደረጉ ተኩሶች በሲቪል ሰዎች ላይ ጉዳት የማስከተላቸው እድል ሰፊ በመሆኑ ኮሚሽኑ ያቀረበውን ምርመራ መነሻ በማድረግ መክላከያም የደረሱ ተጓዳኝ ጉዳቶችን በማጥናት በቀጣይ አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ ይሆናል።

ከድሮን ጥቃት ጋር በተያያዘ ኢላማን ለይቶ በመምታት ረገድ የጎላ ስህተት የማይፈጠር ቢሆንም ከወታደራዊ ጠቀሜታቸው አኳያ ኢላማ በተደረጉ ቦታዎች(ተቋማት) ላይ የደረሰ ተጓዳኝ ጉዳት ካለ በተቋሙ ምርመራ የሚረጋገጥ እና አስፈላጊው እርምት የሚወሰድበት ይሆናል።

5. በታህሳስ ወር 2014 ዓ/ም የመጀመሪያው ሳምንት ማንነታቸው ባልታወቀና ሲቪል በለበሱ 30 ሰዎች ላይ በአማራ ክልል ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ጻዋ ጨፋ አካባቢ ሰዎችን በመደብደብ እና በማሰቃየት በመክላከያ ሰራዊቱ ተረሽነዋል፤ በሰንበቴ ከተማ የአነሃ ሽጌ አባላት ናችሁ በተባሉ አራት ነዋሪዎች ላይም ግድያ ተፈፅሟል በሚል በምርመራው ላይ ቀርቧል።

ይህ ጉዳይ እስካሁን በመክላከያ በኩል ምንም አይነት መረጃ የሌለ ቢሆንም ድርጊቱ ስለመፈፀሙ እና በማን እንደተፈፀመ ጥልቅ ምርመራ ማድረግ የሚያስፈልግ በመሆኑ መክላከያ በቀጣይ ጉዳዩን የምርመራ ቡድን በማዋቀር የሚያጣራው ይሆናል።

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዝርዝር የምርመራ ውጤት ያቀረበ በመሆኑ ለቀረቡት አያንዳንዱ የመብት ጥሰቶች ተገቢውን ማስረጃ ለማቅረብ ጊዜው በቂ ባለመሆኑ በቀጣይ አስፈላጊውን ዝግጅት በማድረግ የሚጣራት ስራውን በመስራት ሪፖርት የምናደርግ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

[redacted]

እንዲያውቁት

- ለክቡር የመክላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር
- ለክቡር የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም

አዲስ አበባ

አባሪ 9

ከጤና ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ



ጤና ሚኒስቴር-ኢትዮጵያ
የዜጐች ጤና ለሀገር ብልፅግና!

Ministry of Health - Ethiopia
Healthier Citizens for Prosperous Nation!

ቀን 10-06-2014
Date
ቁጥር ጤ99/45/05
Ref. No.

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡ በአማራና አፋር ክልል በጤና መሰረተ ልማት የደረሰዉን ጉዳት ሪፖርት ስለመላክ

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከመስሪያ ቤታችሁ ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ሰመኮ/21/ 46/2014 በተጻፈ ደብዳቤ በአማራና በአፋር ክልል በኮሚሽኑ በኩል ምርመራ መደረጉ ተጠቅሶ የጤና ሚንስቴር በጤናው ስርዓት ላይ ስለደረሰዉ ጉዳት በኮሚሽናችሁ ለተለዩ ጥያቄዎች ምላሽና አስተያየት እንድንልክ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

በመሆኑም በጤናው ስርዓት ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚያመላክት አጭር ሪፖርት 7 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡


ከሰላምታ ጋር

[redacted]

ሊያ ታደሰ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

ግልባጭ/
- ለሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለድንገተኛና ጽኑ ህመ.ማን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
ጤና ሚኒስቴር

+251-115-517011
+251-115-518031
+251-115-159657
+251-115-524549
+251-115-516378
+251-115-513301
Fax +251-115-519366
1234
Addis Ababa, Ethiopia
E-mail: moh@moh.gov.et
Website: www.moh.gov.et
Ministry of Health, Ethiopia
@FMoHealth
አባክዎን መልስ ሲሰጡ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ
In Reply Please Refer to Our Ref.No.



በአማራና አፋር ክልሎች በሚገኙ የጤና መሰረተ ልማት ላይ የደረሰ ጉዳት አጭር ሪፖርት

መግቢያ

በአሸባሪዉ ህውሃት ቡድን በተሰነዘረ ጥቃት በአማራ እና አፋር ክልሎች በሰው እና በንብረት ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ ዉድመት እንደተከሰተ ይታወቃል። በአጠቃላይ ጦርነቱ በነበረባቸው አከባቢዎች

- **በአማራ ክልል 3164 ጤና ተቋማት** (502 ጤና ጣቢያ፤ 53 ሆስፒታል፤ 2027 ጤና ኬላ)
- **በአፋር ክልል 340** (339 ጤና ጣቢያና 2 ሆስፒታል) ከ 9.5 ሚልዮን ብር በላይ የሚገመቱ ጤና ተቋማት
- አማራ 8.5 ሚልዮንና
- በአፋር ክልል ከ970 ሺ በላይ ለሚሆን የሕብረተሰብ ክፍል አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ይገኛሉ።

የፌደራል ጤና ሚንስቴርና ክልል ጤና ቢሮዎች በተዘረጋው የጤና ስርዓት የህክምና ግብዓትና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ለህብረተሰቡ የጤና አገልግሎቶች ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ የመድሃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ማከማቻና ማሰራጫ፤ የደም ባንክ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትና የሀብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጦርነቱ በነበረባቸው አከባቢዎች ለማህበረሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እንደነበሩ ይታወቃል። በአጠቃላይ በጦርነቱ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ከደረሰባቸው ሴክተሮች ጤና አንዱ ሲሆን በተለያየ ጊዜ በተደረጉ የመስክ ምልከታና ከክልል ጤና ቢሮዎች የደረሱን ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ የደረሰዉ ጉዳት እንደሚከተለው ቀርቧል።

በጤና መሰረተ ልማት ላይ የደረሰዉን ጉዳት ለመለየት የተሰሩ ስራዎች

በከፍተኛ የጤና ሚንስቴር አመራሮችና በባለሙያዎች በተለያዩ ግዜዎች ጉዳት በደረሰባቸው የጤና ተቋማት ላይ የመስክ ምልከታ ማድረግ ተችሏል በወቅቱም በሺደዮና በሮቶግራፍ የተደገፈ መረጀ ማስቀረት ተችሏል።

- ደብረሲና፤ ሸዋ-ሮብት፤ አጣቤ፤ ከሚሴ፤ ኮምቦልቻ፤ ደሴ፤ ሀይቅ፤ ደበርቅ፤ አዲርቃይ (ዛሪማ ጤና ጣቢያ)፤ ጉፋስ መዉጫ፤ ጋሻን
- በአፋር ክልል ካሊዋን ሆስፒታል፤ ጭፍራ ሆስፒታል፤ ካሳኒስታ፤ ጎሊና፤ እልዋና ያሉ ወረዳ የመስክ ምልከታ በማድረግ መረጀዎችን መሰበሰብ ተችሏል።

- ከአማራና አፋር ክልል በተለያዩ ግዚያት በጤና ተቋማት ላይ የደረሰዉን ጉዳት የሚያሳዩ ሪፖርቶች መቀበል ተችሏል።

- በተመረጡ ጤና ተቋማት ላይ የዳሰሳ ጥናት ባለሙያዎችን በማሰማራት መስራት የተቻለ ሲሆን አሁን ላይ ሁሉንም ጤና ተቋምት የሚዳስስ ጥናት ለማድረግ ዝግጅት ተደርጓል።

በጦርነቱ ምክንያት በጤና ስርዓት ላይ የደረሰው ጉዳት

የአሸባሪዉ ህውሃት ቡድን በወረራ ይዞ በቆየበቸው ግዜዎች በጤናው ስርዓት ከፍተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰ ሲሆን ይህም ለህብረተሰቡ ይሰጥ የነበረዉን የጤና አገልግሎት እንዲስተጓጎል በማድረግ ለህመምና ሞት እንዲዳረግ አድርጎ አልፏል። በሌላ በኩል በጦርነቱ ምክኒያት ከፍተኛ የሆነ የህብረተሰብ ክፍል የተፈናቀለ ሲሆን ይህም በጤናው አገልግሎት ከጦርነት ቀጠና ውጭ ባሉ አካባቢዎች ከፍተኛ የሆነ ጫና እና ህብረተሰቡንም ለተለያዩ ተላላፊ ለሆኑ በሽታዎችና ለምግብ እጥረት እንዲጋለጥ አድርጓዋል። በተጨማሪም በሺዎች የሚቆጠሩ የጤና ባለሙያዎች በጦርነቱ ምክንያት ተፈናቅለው የነበረና ቤት ንብረት የወደመባቸው ሲሆን አካላዊና የስነልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል። በተመሰሳይ በጦርነቱ ከፍተኛ የሆነ የህብረተሰብ ክፍል ለስነልቦናና ስነ-አዕምሮ ጤና መቃወስ እንደሁም ለጾታዊ ጥቃት ተዳርጓል።

በጤና መሰረተ ልማት የደረሰው ጉዳት

- እስከአሁን ባለው መረጀ መሰረት **በአማራ ክልል 1850** ጤና ኬላ፤ **453 ጤና ጣቢያና ፤ 40 ሆስፒታል ፤ በአፋር ክልል 45** ጤና ኬላ፤ **19 ጤና ጣቢያና 2 ሆስፒታል** ላይ ጉዳት ደርሶ አግልግሎት መስጣት አቋርጣዋል።
- ከዚህ በተጨማር በደሴ የሚገኝ የ መድሃኒት ማከማቻና ማሰራጫ፤ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፤ የደም ባንክ ላይ ጉዳት መደረሱን መመልከት ተችሏል።
- በአጣቃላይ **234 (በአማራ 131፤ በአፋር 29፤ ብ.ጉሙዝ 39፤ ኦሮሚያ 6)** የሚሆኑ አምቡላንሶች ተዘርፈዋል ወይም ከአገልግሎት ውጭ ሆነዋል።
- በአጣቃላይ ጉዳት በደረሰበቸው ጤና ተቋማት ዉስጥ የሚገኙ የህክምና መሰርያዎች፤ መድሃኒት፤ የቢሮ እቀዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳትና ስርቆት እንደደረሰ ከመስክ ምልከታና ከተለያዩ የደሰሳ ጥናቶች መረዳት ተችሏል።

ሰሜን ጎንደር በተደረገ ዳሰሰ የተገኙ መረጀዎች

በአማራ ክልል ጤና ቢሮ በኩል ከወረራ ነጻ በሆኑ አካበቢዎች ዳሰሳ የተደረገ ሲሆን ከነዚህም አካበቢዎች ሰሜን ጎንደር ዞን አዲአርቃይ ወረደና በደባርቅ ወረዳ በሚገኙ ዘሪማ ድብ ባህር ጤና ጣቢያ በስራችው የሚገኙ ዘሪማ ጤና ኬላና ድብ ባሂር ጤና ኬላ የመስክ ምልከታ ከተደርገበቸው ተቋማት ይገኙበተል። በወቅቱ በተደረገው የዳሰሳ ምልከታ የተገኙ መረጀዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

በዳሰሳ ወቅት የታዩ መረጀዎች

- በጤና ጣቢያው የህንጻ ግንበታ ላይ የሚታይ ጉዳት የደረሰ ባይሆንም የሁሉም ክፍሎች በርና መስኮት እንደተሰበረ ማየት ተችሏል።
- በጤና ጣቢያው የነበረ ጀነሬተር ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ዉጭ ሆኑዋል።
- የእንግዴ ልጅና የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ(incinerator) ጉዳት ደርሶበቸዋል።
- ለተጨማሪ ብሎክ መገንቢያ የሚሆኑ ተገዝተው ስቶር የነበሩ የግንበታ እቃዎች ሙሉ በሙሉ ተወስደዋል።
- የህክምና ግብዓትና መድሃኒት ሙሉ በሙሉ ወድመዋል አልያም ተሰርቀዋል።

በአጣቃላይ በሁለቱም ወረዳዎች ግምቱ 29,062,762.49 (በዛሪማ ጤና ጣቢያ ብቻ 21,822,823.97) የሚገመት የህክምና መሳርያ፤ መዲሃንት፤ የቢሮ እቀዎች ላይ ዉድመት እንደደረሰ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ያሳያል።



Figure 3 Sample of damaged OR medical equipment in Zarima HC, September

Figure 2: Sample of damaged infrastructures in Zarima HC, Adi'Arkay woreda, September, 2021



Figure 2 Sample of destructed printers and patient cards in Zarima HC, Adi'Arkay woreda



Figure 4 Sample of damaged MCH unit in Zarima HC, September 2021

ሰሜን ወሎ ዞን

በሰሜን ወሎ ዞን በ መቄት ወረዳ በሚገኙ ሸዶ መቄት ሆስፒታል፤ በፈለቅት ፤ በአግሪጤና ደብረዘቢት ጤና ጣቢያና በመቄት ወረዳ በአሻባርዉ ህወሃት ቡድን የደረሰዉን ጉዳት መጠን መመልከት የተቻለ ሲሆን መረጃዎዉም እንደሚከተልው ቀርቧል።

በመቄት ወረደ በሚገኙ በጤና ተቋማት የደረሰ ጉዳት

- የጤና ተቋማቱን እንደ ካምፕ ሲጠቀሙበት እንደነበረ ማየት ተችሏል።
- የጤና ተቋማት ግርግዳዎች ላይ አጻያፍ ስድቦችንና የተለያዩ የፖለቲካ ይዘት ያላቸዉን መልዕክቶች ተጽፈው ተገኝተዋል።
- ከአግሪጥ ጤና ጣቢያ በስተቀር ጄነረተር ከሁሉም ጤና ጣቢያና ሆስፒታል ተወስዷል።
- በሁሉም ጤና ተቋማት የሀሙማን መረጀ ተቃጥሏል አሊያም እንዲበተን ተደርጓል።
- በሁሉም ጤና ተቋማት ዉስጥ የነበረ ከምፒውተሮች፤ ፕሪንተርና ሌሎች ግብዓቶች ወድመዋል።
- የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒት ሙሉ በሙሉ ወድመዋል አልያም ተሰርቀዋል።

በአጠቃላይ በመቄት ወረደ በሚገኙ ጤና ተቋማት (1 ሆስፒታል፤ 5 ጤና ጣቢያና 18 ጤና ኬላ) ግምቱ **71,401,548.42** የሚገመት የህክምና መሳርያ፤ መድሃኒት፤ የቢሮ እቀዎች ላይ ዉድመት እንደደረሰ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ያሳያል።



Figure 4. Looted laboratory unit in Felakit Hospital. September.

Figure 3. Damaged and looted Felakit health center drug store.

በአፋር ክልል በአሻባሪው ህዋሃት ቡድን የደረሰ ጉዳት

በአፋር ክልል በአጣቃላይ በበአሸባርው ህዋሃት ቡድን በ1 ሆስፒታል 24 ጤና ጣቢያና 59 ጤና ኬላ ላይ ጉዳትና ስርቆት እንደተደረገ ማወቅ ተችሏል።

የደረሰው ጉዳት ዝርዝር

- ከልዋን ሆስፒታሉ ዉስጥ የነበሩ የህክምና መሳርያዎችና መድሃኒት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ወድሟል።
- የቢሮ እቃዎች፤ ከምፕዉተሮችና የጽህፈት መሳሪያ እንዲወድም ተደርጓል።
- የታካሚዎች የህክምና መረጀዎች ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን ተደርጓል።
- በአዉራ ወረዳ የሚገኝ ሂደት ጤና ጣቢያ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን በአዲስ መልክ መገንባትና ማሳደስ ይፈልጋል።
- በእዋ ወረዳ የምገኝ አልሱበል ጤና ጣቢያ የህክምና መሳርያ፤ መድሃኒትና የተለያዩ የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎች ሙሉ በሙሉ ወድመዋል።

በተደረገው ዳሰሳ የደረሰው ጉዳት በገንዘብ ሲተመን በካልዋን 153,913,758፤ በእዋ 35,059,656 እና በየሎ ወረዳ 48,358,156 መሆኑን ከክልል ጤና ቢሮ የተገኘው የደሰሳ ሪፖርት ያሳያል።



በጤና ሚንስቴር የጤና ስርዓቱን መልሶ ለመቋቋም የተሰሩ ስራዎች

የጤና ችግር ግዜ የሚሰጥ ከለመሆኑ በጦርነቱ አገልግሎታቸው ተቋርጦ የነበሩ ጤና ጣቢያዎችንና ሆስፒታሎችን ከአዲስ አበባ ሆ/ሎች፤ ከዩንቨርሲቲና ከፌዴራል ሆስፒታሎች፤ ከክልል ጤና ቢሮዎች ፣ ከመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም ከግል ማኅበራት ጋር በመተሳሰር መሰረታዊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ለማስጀመር ሰፊ ስራ ተሰርቷል። በዚህ ትስስርና በክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በቅንጅት በተሰራ ስራ በ36 ሆስፒታሎች፤ 290 ጤና ጣቢያና ከ890 በላይ ጤና ኬላዎች መሰረታዊ የሆኑ የህክምና አገልግሎቶችን ማስጀመር ተችሏል። በተፈጠረው ትስስር አማካይነት ከ120 ሚልዮን ብር በላይ የምገመት የመድሃኒትና የህክምና መሳርያዎች ድጋፍ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ በአምቡላንሶች መጎዳት የሚፈጥረውን ጫና ታሳቢ በማድረግ 13 አምቡላንሶች ድጋፍና ከዚህ በፊት በተለያየ ብልሽት ቆመው ከነበሩ አምቡላንሶች 64 ተጠግነው ለአገልግሎት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

በተጨማሪ እስካሁን ድረስ ከፌደራል ጤና ሚንስቴር ከ660 ሚልዮን ብር በላይ የሚገመት መድሃኒትና የህክምና መሳርያዎች ድጋፍ ጦርነት በተከሰተበቸው አካባቢ ላሉ ጤና ተቋማት ድጋፍ ተደርጓል። በተመሳሳይ መልኩ ለተፈናቃይ ወገኖች በተጠለሉበት ማዕከላት የጤና አገልግሎት ለማድረስ ጊዜያዊ ክሊኒኮች በማደራጀትና በአቅራቢያ ከሚገኙ ጤና ተቋማት ጋር በማስተሳሰር የጤናና ስርዓተ ምግብ አገልግሎት እንድሰጡ የተደረገ ሲሆን ተደራሽ ላልሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ደግሞ ከ65 በላይ ተንቀሳቃሽ የጤናና ስርዓተ ምግብ ቡድኖች (Mobile Health and Nutrition Team) በማደራጀት እና በማሰማራት መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ተደረሽ የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

በሌላ በኩል በጦርነቱ የስነልቦናና ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ የጤናና ስነ አዕምሮ ጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ወደ 16 በሚሆኑ ማዕከላትና ጤና ተቋማት ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ወገኖቻችን አስፈላጊውን ህክምናና ድጋፍ እየሰጡ ሲሆን የስነ ልቦናና የተለያዩ የሰነ አእምሮ ጉዳት ለደርሶባቸው የህክምና አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። ይህንን ሥራ በስፋት መስራት ያስችል ዘንድ ከሰራተኛና ማህበራዊ ሚንስቴር ጋር የጋራ እቅድ በማዉጣት እየተሰራ ይገኛል። ለ270 ባለሞያዎችም የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል።

በአጠቃላይ ጤናው ዘርፍ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የጤና አገልግሎት ስርዓቱን ወደ ነበረበትና ወደ ተሻለ ደረጀ ለመመለስ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ የሁሉም ባለድርሻ አካላትን ሰፊ ተሳትፎ የሚጠይቅ ሲሆን ጤና ሚንስትርም ሁሉንም በማስተባበር ***ጠንካራና የተሻለ*** የጤና ስርዓት በፍጥነት ለመገንባት ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል።

አባሪ 10

ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠ ምላሽ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፖ.ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: 29/6/2014
ቁጥር/REF NO: 66/2-6412/2006-2135

ለኢትዮጲያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በአማራና አፋር ክልሎች በትም/ት ተቋማት ላይ የደረሰውን ጉዳት ይመለከታል።

ከላይ በርእሱ እንደተገለፀው ዋር 27/2013 ዓ.ም በቁጥር ሰመከ/2-1/52/2014 ለመስሪያ ቤታችን በተጻፈ ደብዳቤ በአማራና አፋር ክልሎች የግጭት አካባቢዎች የትምህርት ተቋማትና የትምህርት አገልግሎት አቅርቦት ሁኔታ፤ በግጭቱ አካባቢዎች በትምህርት ተቋማት ላይ ስለደረሰ ዝርፊያና ውድመትን አስመልክቶ ይህንን ለማጣራት ስለተወሰደ እርምጃ እና በግጭት አካባቢዎች ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለተደረገ ድጋፍ በተመለከተ ሪፖርት እንድናቀርብ በተጠየቅነው መሰረት 26 ገፅ ሪፖርት አዘጋጅተን በዚህ ሸኚ ደብዳቤ የላክን መሆኑን እንገልፃለን።


ከሰላምታ ጋር

[redacted]

ኤልያስ ገርማ ዋቅጅራ
የፅድ ዝግጅትና ሀብት ማፈለማ
ዳይሬክተሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ:-
- ለክቡር ሚኒስትር ፅ/ቤት
- ለክቡር የአጠቃላይ ትምህርት ሚኒስትር ዲኤታ
- ለክቡር የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዲኤታ

ትምህርት ሚኒስቴር



ማጠቃለያ መረጃ

ትምህርት ሚኒስቴር ግጭት በተከሰተባቸው በተለይ በአማራና በአፋር ክልሎች የጉዳቱን መጠን ለማጥናት በሁለት ዙር ባለሙያዎችን ወደ ክልሎቹ በማሰማራት ከክልሉ ት/ቢሮ፤ የእዱጋ ስጋት መ/ቤቶች፣ ሌሎች ሚኒስትር መ/ቤቶችና የልማት አጋሮች ጋር በመሆንሩ

- የጉዳት መጠን ጥናት (Rapid Assessment) አካሂዱልኗ የተገኘውን የጥናት መነሻ መረጃ በማደራጀት የእዱጋ ጊዜ ትምህርት የማስጀመር እቅድ አዘጋጅቷል።
- የእቅድ ማስፈጸሚያ በጀት ለማግኘት ከልማት አጋሮች ጋር ውይይት ተጀምሯል።

ይህን የሚያስፈጽም የትምህርት ሚኒስቴር የእዱጋ ጊዜ ትምህርት የማስጀመርና የማስተጠል ኮሚቴ ተቋቁሟል። በዚህም መሰረት የተገኘ ግኝቶች እንደሚከተለው ይቀርባል።

ሀ. በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ

ክልል	ሙሉ በሙሉ የወደሙ ት/ቤቶች	በከፊል የወደሙ ት/ቤቶች	ከትምህርት ገበታ ውጭ የሆኑ ተማሪዎች	የተፈናቀሉ መምህራን
አማራ	1025	3,082	1,896,819	116,939
አፋር	65	138	49,697	4,376
ጠቅላላ	1090	3,220	1,946,516	121,315

ለ. በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ

ዩኒቨርሲቲዎች	ከትምህርት ገበታ ውጭ የሆኑ ተማሪዎች	የተፈናቀሉ መምህራን	የአስተዳደር ሰራተኞች
ወልድያ	15,300	1,216	987
ወሎ	26,204	2,036	1,650
መቅደላ አምባ	5288	430	556
ጠቅላላ	46,792	3,682	3,193

በአጠቃላይ በትምህርት ልማት ዘርፍ አሸባሪው ህይል በመሰረተ ልማት ላይ ካደረሰው ጉዳት በተጨማሪ ከ2 ሚሊዮን በላይ በሚሆኑ ተማሪዎችና መምህራን ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የስነልቦና ጉዳት እንዲሁም ማህበራዊ ቀውስ ፈጥሯል። ለአብነትም ትምህርት ተቋማትን የወታደር ካምፕ አድርጎ መጠቀም፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች የማውደም (ከሸካ ማንኪያ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የቴክኖሎጂና ቤተ መከራ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎች ወዘተ)፣ የተማሪዎች

1

አስተዳዳራዊና አካዳሚክ ሰነዶች ማውደም፤ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የጅምላ መቃብር ቦታ ማድረግ ለአብነትም እስከአሁን ከ40 በላይ የሁለተኛ ደረጃና ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የጅምላ መቀብሮች መገኘታቸው የመሳሰሉት ጉዳቶች ደርሰዋል።

የጉዳቱ ሁኔታ የረዥም ጊዜ የትምህርት ዕድል እጦትን እያስከተለ በመሄዱ በነዚህ ክልሎች ያሉ ህጻናት ከፍተኛ የትምህርት ኪሳራ ደርሶባቸዋል፤ ይህም የህጻናቱ ትምህርት አለማግኘት በቀጣይ ሀገር ተረክቢ ትውልድ የማፍራት ሁኔታን ጥያቄ ውስጥ ያስገባል፤ ዘላቂ ተጽእኖ ይኖረዋል። ትምህርት ቤቶች ረዘም ላለ ጊዜ ሲዘጉ፣ ትምህርት የማቋረጥ አድላቸው እየጨመረ ይሄዳል፤ ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ እድላቸው እየጠበበ ይመጣል። በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ውጪ የሆኑ ልጆች ለሥጋትና እንግልት የበለጠ ተጋላጭ ይሆናሉ፤ ጾታዊ እና ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ሰለባ ይሆናሉ፤ ከትምህርት ይልቅ ለጦርነት የመመልመል እድላቸው ይሰፋል፤ የህጻናት ጥቃት ከመስፋፋቱም በላይ ያለእድሜ በህጻንነት ያለዕድሜ እርግዝና እና የልጅ ጉልበት ብዝበዛ ይስፋፋል። ትምህርት ቤቶች ሲዘጉ ህጻናት የአእምሮ ጤና እና ስነ-ልቦናዊ ማህበራዊ ቀውስ ይከሰታል፤ አመጋገብ እና የትምህርት ቤት መመገብን ጨምሮ ሌሎች ወሳኝ አገልግሎቶችን እንዳያገኙ ያደርጋል።

ስለሆነም አሁን የተፈጠረውን የወራሪ ሀይል ከሁለቱ ክልሎች የማስወጣትና ድንበር የማስከበር ስኬት መነሻ በማድረግ ልጆች የመማር ክህሎቶቻቸውን እንዲያጸብሩ፤ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ እንዲኖሩ ለማስቻል፤ በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ አስደንጋጭ ቀውስን ለመቋቋም ድጋፍ መደረጉን ለማረጋገጥ፤ አወንታዊ የመቋቋሚያ ዘዴዎችን ለማዳበር እና የህይወት ዘመንን ለመደገፍ አስፈላጊ ክህሎቶችን ለማግኘት የበለጠ ወሳኝ ነው።

1. በአማራና አፋር ክልሎች የግጭት አካባቢዎች የትምህርት ተቋማትና የትምህርት አገልግሎት አቅርቦት ሁኔታ በተመለከተ

1.1. አፋር ክልል

በክልል ላይ በተደረገው ወረራ ብዛታቸው በአራት ዞኖች የሚገኙ 759 ትምህርት ቤቶችና 21 የወረዳ ትምህርት ፅ/ቤቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጎጂ በመሆናቸው በእነዚህ የትምህርት ተቋማት ይካሄድ የነበረው የመማር ማስተማሩ ስራ ተቋማቱ በመደማቸው፤ የጦር ካንፕ በመሆናቸው እና የተፈናቃይ መጠለያ ሆነው በመቆየታቸው የትምህርት አቅርቦቱ እስከ ታህሳስ ወር 2014ዓም ድረስ ተቋርጦ የቆየ ቢሆንም ትምህርት ሚኒስቴርና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ባደረጉት የተቀናጀ ድጋፍና ተቋማትን መልሶ ወደ መደበኛ ስራቸው ለመመለስ በተፈጠረ የህብረተሰብ ንቅናቄ በወደሙ ትምህርት ቤቶች ለጊዜዊ የመማሪያ ክፍልነት የሚያገለግሉ የድንኳኖችን ከዩኒሴፍ በተገኘ ድጋፍ በየተምህርት ቤቱ እንዲተከሉ በማድረግ ተቋርጦ የነበረው ትምህርት ከነ ሙሉ ጉድለቱም ቢሆን እዲጀምር ለማድረግ ከክልል ትምህርት ቢሮና ከትምህርት ሚኒስቴር የተውጣጣ ግብረሃይ በህብረተሰቡ ውስጥ አስፈላጊው ቅስቀሳ በማድረግ የማሰማራት የመማር ማስተማሩን ለማስጀመር የሚያስፈልጉ የመጀመሪያና መሰረታዊ ግብአቶች ማለትም ጠመኔ ጥቁር ሰሌዳ የተማሪ ደብተርና እስከሪፕቶ በክልሉ በኩል ተገዝተውና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ድጋፍ በማሰባሰብ ለትምህርት ቤቶችና ለተማሪዎች በተደረገ ድጋፍ ለወረራው ተጋላጭ በነበሩ 4 ዞኖች የማስጀመር ስራ የተከናወነ ሲሆን ካለጦርነት መናር የማይችለው የህውሃት ወራሪ ቡድን በዞን ሁለት በሚገኙ 6 ወረዳዎች ላይ በፈፀመው ዳግም ወረራ ትምህርት ቤቶቹ ለዳግም ጥቃትና ጥፋት በመጋለጣቸውና ከሶስት መቶ ሺህ ህዝብ በላይ በመፈናቀሉ የትምህርት አቅርቦት አገልግሎቱ የተቋረጠ ቢሆንም በዞን አንድ አራትና አምስት የመማር ማስተማሩ ሂደት እዲጀምርና እዲቀጥል የተደረገ ሲሆን በቅርበት ለመደገፍ እንደቻል ትምህርት ሚኒስቴር 7 የልዩ ድጋፍ ባለሙያዎች ከሁለት ተሽከርካሪ ጋር በማሰማራት ከክልል ትምህርት ቢሮ ጋር ተቀናጅቶ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል ::

1.2. አማራ ክልል

ወላጆች /ህብረተሰቡ/ የትምህርት ስራ እንዲጀመር ከፍተኛ ፍላጎት ያለው መሆኑ እና በጦርነቱ ጉዳት ለደረሰባቸው የትምህርት ተቋማት ማደሻ በጀት ከትምህርት ሚኒስቴር፤ ከአጋር አካላትና

ትውልደ ኢትዮጵያኖች ሊገኝ መቻሉ፤ በአብዛኛው ለመጠለያነት ያገለገሉ ትምህርት ቤቶች መለለቀቅ፤ ማስጠገንና በማዕዳት የመማር ማስተማር ስራ ማስጀመር መቻል እንዲሁም በተወሰነ መልኩ ቢሆንም ለተማሪዎች የኒፎርምና የትምህርት ቁሳቁስ ማቅረብ፤ ሙሉ በሙሉ እና በከፊል ለወደሙ ትምህርት ቤቶች ጊዜያዊ መማሪያ ክፍሎችን ማዘጋጀት። ዕድሳት የሚያስፈልጋቸው የትምህርት ተቋማት መለየታቸው እና የክልል ትምህር ቢሮ የትምህርት ስራውን ለማስጀመር የሚያስችል የሰው ሃይል ማዘጋጀት፤ ለመምህራንና ተማሪዎች እነዲሁም ለትምህርት ባለሙያዎች የስነ-ልቦና ስልጠና መስጠት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና በመስጠት የስነ-ልቦና አቅም እንዲያዳብሩና ወደስራ መመለሳቸው።

የትምህርት አመራሩ የትምህርት ስራ በቁርጠኝነት እንዲጀመር ማድረግ እና የተለያዩ ድርጅቶችን ተደራሽ በማድረግና የተፈጠረውን ችግር በመስረዳት በጀት ማፈላለግ፤ ለመምህራን ማንዛቤ በመፍጠርና የስነ-ልቦና ስልጠና በመስጠት ለመማር ማስተማር ስራ ማዘጋጀት መቻል። ለወላጆች ግንዛቤ መፍጠር እና የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም የተማሪ ቅስቀሳ ማድረግ፤ የትምህርት ቤት ምገባ መጀመርን ጨምሮ ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ እና የኒፎርም ማሟላት መቻል። ለመጠለያነት ያገለግሉ ትምህርት ቤቶችን በማስለቀቅ እና ህብረተሰቡን በማሳተፍ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለወደሙባቸው አካባቢዎች ጊዜያዊ መማሪያ ክፍሎችን ማዘጋጀትን ጨምሮ ትምህርት ቤቶችን በፍጥነት በመጠገን ወደ ስራ ማስገባት ተችሏል።

2. በግጭቱ አካባቢዎች በትምህርት ተቋማት ላይ ስለደረሰ ዝርፊያና ውድመት በተመለከተ ይህንን ለማጣራት ስለተወሰደ እርምጃ

2.1. አፋር ክልል

በአፋር ክልል ካሉ ስድስት ዞኖች በዞን 1፤2፤4 እና 5 ወረራ የተፈፀመባቸው ዞኖች ሲሆኑ 150,754 (45% ሴ) ተማሪዎችን፤759 ት/ቤቶች እና 21 ወረዳዎችን በጦርነቱ ምክንያት በቀጥታና በተዘዋሪ ጉዳት አድርሷል።በተጨማሪም 6156 (24.6%) መምህራንን ከስራ ቦታ በማፈናቀልና ህብትና ንብረት በማሳጣት ጉዳት አድርሷል። በዚህም በጦርነቱ ሙሉ በሙሉ የወደሙ ት/ቤቶች ብዛት 65 በከፊል ጉዳትባቸው ት/ቤቶች ብዛት 138 የተፈናቃይ መጠለያ የሆኑ ት/ቤቶች 52 የጦር ካምፕ የነበሩ ት/ቤቶች 62 ጉዳት በደረሰባቸው ት/ቤቶችና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች በውስጣቸው የሚገኙ የትምህርት መረጃዎች፤ኮምፒዩተሮች ፤

ወንበሮች፤ጠረጴዛዎችና መቀባየ ማሽኖችና ደክመንቶች የሚፈልጓቸው ተወስደዋል። ሌሎች ወድመዋል፤እንዲበላሹ ሆነዋል።ከዚህም ጋር ተያይዞ የጽ/ቤት ባለሙያዎችና መምህራን መኖሪያ ቤቶች በመዘረፋቸው ንብረት አልባ ሁነዋል። በአነዚህ አካባቢዎች በሚገኙ በትምህርት ተቋማት የማህበረሰብ አካላት እና ንብረት የደረሰውን ውድምትና ጥፋት ለማጣራትና ለማየት ክቡር የትምህርት ሚኒስቴሩ ከክልሉ ጋር በመሆን በአካል ተገኝተው የጉዳቱን ስፋት መጠን በመመልከት በቀጣይ መደረግ መሰራት ባለባቸው ተግባራት ላይ አቅጣጫ አስቀምጠዋል መልሶ ለመገንባትና ለማደራጀት ህብት የማሰባሰብ ስራ ተጀምሯል ። ከትምህርት ሚኒስቴር ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ያለውን ጉዳት ለማጣራትና መረጃ ለማሰባሰብ እንዲሁም ት/ቤቶች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነውም ትምህርት ለማስጀመር ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ለማድረግ የልዩ ድጋፍ ባለሙያዎችን ከተሸከርካሪዎች ጋር በመመደብ ከክልሉ ጋር ተቀናጅቶ የመደገፍና የማስተባበር ስራ ተሰርታል በዚህም የጉደሉቱን አይነትና መጠን የመለየት ስራ ተሰርታል።

2.2. አማራ ክልል

አሸባሪው የትህነግ ቡድን በአማራ ክልል በከፍተኛ ደረጃ በመስፋፋት ወረባቡን ጨምሮ በደረሰባቸው ሁሉም ወረዳዎች ከፍተኛ የሆነ ሰብአዊና ቁሳዊ ጥፋት በማድረስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው በማፈናቀል ለከፍተኛ ረሀብ እና ችግር ተጋልጠዋል። በዚህም ሴቶች ተደፍረዋል፤ በጫካ ወልደዋል፤ በየጫካ ሞተዋል እንዲሁም ቤታቸው ተቃጥሏል።

አሸባሪ ቡድኑ ምንም እንኳን በሁሉም የመንግስትና የግል ተቋማት ላይ ጥፋት ቢያደርስም በትምህርት ተቋማት ላይ ያደረሰው ጥፋት በጣም ከፍተኛ ነው። እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት በክልሉ 1,660 (277 ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ሲወድሙ 1,383 ትምህርት ቤቶች በከፊል) ወድመዋል። የአንደኛ ደረጃ፤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ሁለት የመምህራን ኮሌጆች ጉዳት ደርሶባቸዋል። 1.2 ሚሊዮን ተማሪዎች እና 47,000 መምህራን የጉዳቱ ሰለባ ሆነዋል። ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ቤቶች የመጠለያ ጣቢያ በመሆን ከፍተኛ የሆነ ጉዳት እየደረሰባቸው እና ለመማር ማስተማር ስራው አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ፈጥረዋል። በወረዳው 65 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች መጠለያ ጣቢያ ሆነው አገልግለዋል።

ለዚህ ሁሉ ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ ለመስጠት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ለዚህም ተግባር ትምህርት ሚኒስቴር፤ ትምህርት ቢሮ ክዩኒሴፍ እና ከሌሎች መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች

ጋር በመተባበር መረጃዎችን በማደራጀትና የተለያዩ ሀብቶችን በማፈላለግ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል። በትምህርት ቢሮ አስተባባሪነት ትምህርትን በአደጋ ጊዜ ማስቀጠል በሚል ግብረ ሀይል ተቋቁሞ ሳምንታዊ ውይይት በማድረግ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እያስቀመጠ ይገኛል። በዚህም ዩኒሴፍ የስነ-ልቦና ስልጠና በመስጠትና የተለያዩ ድንኳኖችን፣ ወንበሮችን፣ በሮችን እና የፋይ ማቀፊያዎችን ድጋፍ አድርጓል። መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች የስነ-ልቦና ስልጠና እና የተለያዩ ድጋፎችን ለማግኘት የተለያዩ ድርጅቶችን ዩኒቨርሲቲዎችን እየጠየቀ ይገኛል።

3. በግጭት አካባቢዎች ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለተደረገ ድጋፍ

3.1. አፋር ክልል

በአፋር ክልል ላይ በወራሪው የወያኔ ቡድን የደረሰው ውድመትና ዘረፋ ዘርፈ ብዙ ከመሆኑም በላይ በአጭር ጊዜ ወደ ነበረበት ለመመለስ ከፍተኛ ሃብትና ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም የምህርት ስራውን ለማስቀጠል እንዲቻል ከተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶችና አካላት ሀብት የማሰባሰብ ስራ የተጀመረና ድጋፍ ሰጪ አካላት በአነዚህ አካባቢዎች ድጋፎች እንዲያደርጉ የመጋበዝና የትኩረት አካባቢዎች እንዲሆኑ ተከታታይ ስራዎች በመሰራት ላይ ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ለአነዚህ በወረራው ተጠቂ ለሆኑ የትምህርት ተቋማት አገልግሎት የሚውሉ የትምህርት ግብአቶችን ለማሟላት የሚውል አርባ ሚሊዮን /40,000,000 / ለክልሉ መንግስት በመስጠት የተማሪ መቀመጫ ዴስክ ጥቁር ሰሌዳና የተማሪ መቀመጫ ዴስኮች ተገዝተው በወረራው ለተጎዱ ትምህርት ቤቶች እዲሰራጭ ተደርጓል አፈፃፀሙንም በመስክ በመገኘት ድጋፍና ክትትል ተደርጎ ለትምህርት ተቋማቱ መድረሱን ማረጋገጥ ተችሏል ። የወደሙ የትምህርት ተቋማትን በዘላቂነት መልሶ ለመገንባት ከሲጋሽ ድርጅቶች እስከአሁን ብር አንድ መቶ ሰላሳ ሚሊዮን ብር የተሰባሰበ ሲሆን ኩቴሊኩሙኒኬሽ ጋር በመተባበር ሁሉንም ያሳተፈ ሃብት የማሰባሰብ ስራ ተጀምሯል

በአፋር ክልል በተለይ የከፋ ውድመት በደረሰባቸው ትምህርት ቤቶች የመልሶ ግንባታ ለማካሄድ የሚያስችል ከአጋሮች ጋር በመተባበር የዲዛይን ስራ የተጀመረ ሲሆን ጉዳቱ በደረሰባቸው ትምህርት ቤቶችበአካል ተገኝቶ የዲዛይን ስራውን ለመስራት የሚችል ቡድን ተደራጅቶ በገፃችን ላይ ይገኛል።

3.2. አማራ ክልል

ረዘም ላሉ ጊዜያት በሰላም እጦት ምክንያት ከትምህርት ገበታ የተለዩ ተማሪዎችን ደረጃ በደረጃ ወደ ትምህርት ቤት በማምጣት መደበኛውን የትምህርት ስራ ማስቀጠል መቻል። ረዘም ላሉ ጊዜያት በሰላም እጦት ምክንያት ከመማር ማስተማር ስራ የተለዩ መምህራንንና የትምህርት ባለሙያዎችን ወደ መደበኛው ስራቸው ማስገባት መቻል። ረዘም ላሉ ጊዜያት በሰላም እጦት ምክንያት ትምህርት በመቋረጡ ቅሬታ ያላቸው ወላጆችና የአካባቢው ማህበረሰብ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ተችሏል።

ወራሪው ቡድን ወረራ በፈጸመባቸው አካባቢዎች ለትምህርት ማህበረሰቡ (አስተማሪዎችና የትምህርት አመራሩ) የስነ-ልቦና አቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት ወደ መደበኛ የትምህርት ስራ ማስገባት መቻል። ወራሪው ጥቃት ያደረሰባቸውን የትምህርት ተቋማት የጥገና እና የመልሶ ግንባታ ስራ ከሚመለከታቸው አካላትጋር ሀብት በማፈላለግ ማስጠገን እና መስራት። የወደሙትን የትምህርት ተቋማት እና ግብአት ወይም ቁሳቁሶችን እና የቴክኖሎጅ ግብአቶች (ፕላዝማ፣ ራዲዮ የአይሲቲና እንተርኔት) ለሚሟት ውጤታማ የሆነ ልዩ ልዩ ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑ፤ ውድመት የደረሰባቸውን የቤተ-መጻህፍት ቤተ-መጻህፍት መልሶ ለማቋቋምና ለሚሟሉት እንቅስቃሴ ማድረግ መቻል። ለተፈናቀሉ ወገኖችና ለጸጥታ ሃይሎች በመጠለያነት ሲያገለግሉ የቆዩ የትምህርት ተቋማት ለትምህርት አገልግሎት እንዲዉሉ ተደርጓል።


የወደሙ የትምህርት ተቋማት የመማር ማስተማር ስራ በጊዜያዊነት የሚተኩ ጊዜዊ የትምህርት መስጫ ቦታዎችን ማዘጋጀት መቻላቸው። ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው በመጠለያና በዘመድ አዝማድ ተጠግተው ሚኖሩ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የ2013 ዓ.ም ሃገር አቀፍ የመልቀቂያ ፈተና በሁለተኛ ዙር በያሉበት መውሰድ እንዲችሉ ማመቻቸት እና ማስፈን መቻል። የወደሙ የትምህርት መሰረተ ልማቶችን በአንጻራዊነት በመጠገን ወደ አገልግሎት ማስገባት መቻል። ወረራ በተደረገባቸው አካባቢዎች የህበረተሰቡ ሀብትና ንብረት የተዘረፉና የወደመ ቢሆንም ሀብረተሰቡ ለትምህርት ስራ አቅም እንዲሆኑ ግንዛቤ በመፍጠርና በማሳደግ ለተማሪዎች ዩኒፎርም፣ የትምህርት ቁሳቁስ ማቅረብ እና ለ1ኛ ደረጃ ተማሪዎች በተወሰነ መልኩ የትምህርት ቤት ምገባ ማስጀመር ተችሏል።

4. ዝርዝር ኩነቶችና በትምህርት ተቋማት ላይ የደረሰ ጉዳት በመሚመለከት

4.1. አፋር ክልል

ሀ. በጉሊና ወረዳ ጋሊኮማ ቀበሌ

የተፈፀመውን ዘረፋና ውድመት ከትምህርት ሚኒስቴር ከክልሉ ትምህርት ቢሮ ጋር ተቀናጅቶ የተካከ ቡድን ጉዳቱ በደረሰባቸው የትምህርት ተቋማት በአካል ተገኝቶ ባደረገው ማጣራት በጉሊና ወረዳ የትምህርት ፅ/ቤት ላይ በተካሄደ ወረራና ዘረፋ ኮፒዩተሮች ፣ላፕ ቶፖች ፣ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ፣ 5 ሞተር ሳክሎች የተዘረፉ ሲሆን በወረዳው ስር ከሚገኙ 9 ትምህርት ቤቶች ሙሉ ለሙሉ 14 ትምህርት ቤቶች በከፊል በወራሪው ቡድን ዘረፋና ውድመት ተፈፅሞባቸውል እነዚህ ትምህርት ቤቶች በመጋዘን የነበራቸው የተማሪ የምገባ እህልና ዘይት ፣ያላቸው ኮፒዩተሮች ፣ፕሪንተሮችና የላብራቶሪ እቃዎች የተዘረፉ ሲሆን አጠቃላይ የተማሪ መፅሃፍቶችና የትምህርት ቤቶቹ ዶክመንቶች እንዲወድሙ ተደርገዋል :: በተለየ ሁኔታ በጋሉኮማ ትምህርት ቤት ላይ በተፈፀመ የከባድ መሳሪይ ጥቃት ጦርነቱን ሸሽተው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ተጠልለው የነበሩ ንፁሃን ህፃናትና አዛውንት ዜጎቻችን በአሰቃቂ ሁኔታ ሞትና መቁሰል አደጋ እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን ትምህርት ቤቱ የነበሩትን የተማሪ የምገባ እህልና ዘይት ኮፒዩተር የተማሪ መቀመጫዎች የቢሮ ወንበሮችና ጠረፔዛዎች የተማሪ መፅሀፍቶች እና አጠቃላይ ዶክመንቶች የወደሙ ሲሆን ለጥቃት የተጋለጠው አንድ ብሎክ ህንፃ ተመልሶ አገልግሎት መስጠት በማይችልበት ደረጃ ላይ በመሆኑ በከፍኒሴፍ በተገኘ የድንኳን ድጋፍ በጊዜዊ የመማሪያ ክፍልነት እየተጠቀመ ይገኛሉ::





ለ . በአውራ ወረዳ

በአውራ ወረዳ የተፈፀመውን ዘረፋና ውድመት ከትምህርት ሚኒስቴር የተካከ ቡድን ጉዳቱ በደረሰባቸው የትምህርት ተቋማት በአካል ተገኝቶ ባደረገው ማጣራት የወረዳውትምህርት ፅ/ቤት ኮፒዩተሮች ላፕ ቶፖች ፎቶኮፒ ማሽን ሶስት ሞተር ሳይክሎች የቢሮ አጠቃላይ ወንበሮችና ጠረፔዛዎች አጠቃላይ የቢሮ ዶክመንቶች ተዘርፈዋል የማይፈልጓቸው እዲወድሙ ተደርገዋል የህብረተሰቡን ስነ ልቦና ሲጎዳና ወደ ተቋማቱ ገብቶ ለመስራት እዲዘገንናቸው ለማድረግና ፍርሃቻ በሚፈጥር መልኩ የራሳቸውን አስከሬን በትምህርት ፅ/ቤቱ በር ላይ በሁለት ቦታ ላይ ቀብረዋል በወረዳው ውስጥ ከሚገኙ ትምህር ቤቶች መካከል 6 ሙሉ ለሙሉ 15 በከፊል እንዲወድሙ የተደረጉ ሲሆን ስድስት ት/ቤቶች ከተለያዩ አካባቢዎች ጦርነቱን ፈርተው የተፈናቀሉ ዜጎች መጠለያ ሰባቱ ደግሞ የወራሪው ህውሃት ቡድን የጦር ካፕ ሆነው በመቆየታቸው በውስጣቸው ያሉ የመማሪያ ክፍል ንብረቶች ኮፒተሮች የቤተ መከራና ቤተመፅሃፍት ንብረቶች የተማሪዎች ምገባ እህልና ዘይት አጠቃላይ የትምህርት ቤቶቹ ዶክመንቶች ለውድምትና ዘረፋ ተጋልጠዋል::

በተለየ ሁኔታ ደራይቱ ከተማ ላይ በተፈፀመ ወረራ የአውራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አራት ክፍሎች ያለው አንድ ብሎክ ዕንባ በከባድ መሳሪያ ድብደባ ሙሉ ለሙሉ እንዲወድም ተደርጓል:: ትምህርት ቤቱ የነበረው የአይሲቲ ማእከል 35 ኮፒዩተሮች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተተክለው የነበሩ ፕሳዝማ ቴልቪዝኖች የቢሮ ኮፒዩተሮች ፕሪንተር ፎቶ ኮፒ ማሽኖች የቤተመፅሃፍት ንብረቶች ተዘርፈዋል ሌሎች የማይፈልጓቸውን ዶክመንቶችና ምዕሃፍቶች እንዲወድሙ ተደርገዋል ከወደመው አንድ ብሎክ ውጪ ያሉ በሌሎች ክፍሎች ላይ ያሉ በሮችና መስኮቶቻቸው የተሰባበሩና የተነቀሉ በመሆኑ ወደ ስራ ለመመለስ ጥገና ይፈልጋሉ

Awra Secondary school



Awra secondary school



Awera 2ndry school

4.2. አማራ ክልል

ሀ.ወረባቡ ወረዳ

የወረባቡ ወረዳ ትምህርት ተቋማት ላይ የደረሰ ዝርፊያ እና ውድመት የጥፋት ቡድን ወረራ ባካሄደባቸው የወረዳው ቀበሌዎች የሚገኙ ትምህርት ተቋማትን ቴክኖሎጅ ነክ የትምህርት ግብአቶችን ዘርፎ ሲወስድ ሌሎች ግብአቶችን ለአገልግሎት እንዳይዉሉ በማሰብ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ አውድሟቸዋል። ሀንጻዎችንም በከባድ መሳሪያ በመምታት እና በሮችን፣ መስኮቶችን እንዲሁም መስታዎቶችን በመነቃቀልና በመሰባበር ከጥቅም ውጭ አድርጓቸዋል።

አሸባሪ ቡድኑ በወራባቡ ወረዳ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ላይ ከፍተኛ እና አሰቃቂ የሆነ ጥፋት አድርሷል። ይህ አሸባሪ ቡድን በወረባቡ ወረዳ ትምህርት ተቋማት ላይ ባደረሰው ጉዳት የመማር ማስተማር ስራው በከፍተኛ ደረጃ ተጎድቷል። በርካታ ተማሪዎች ተፈናቅለዋል እንዲሁም ከትምህርት ገበታ ውጭ ሆነዋል። የወደሙ እና በከፊል የወደሙ ትምህርት ቤቶች በርካታ በመሆናቸው እና ተማሪዎች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ለማድረግ እና በፍጥነት አቅም በፈቀደ መፍትሄ በማፈላለግ ችግሩ የከፋ ቢሆንም ለመቋቋም ጥረት እየተደረገ ይገኛል። የተለያዩ የትምህርት ተቋማት ንብረቶች ተዘርፈዋል፣ እንዲሁም መሰረተ ልማቶች ወድመዋል።

አሸባሪው ቡድን በዛሪማ ከተማ ብዙ ውድመቶች ያደረሰ ሲሆን ከትምህርት ተቋማት አንፃር:-

- 2(ሁለት) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ሙሉ ለሙሉ አውድሟል።
- 1(አንድ) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ሙሉ ለሙሉ በማውደም ከጥቅም ውጪ አድረጓል። የትምህርት ቤቶቹ ስም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ተ.ቁ	የትምህርት ቤቱ ስም	የጉዳቱ ሁኔታ
1.	ዛሪማ የመጀመሪያ ደረጃ ትም/ት ቤት	ሙሉ ለሙሉ የወደመ
2.	ዛሪማ ሁለተኛ ደረጃ ትም/ት ቤት	ሙሉ ለሙሉ የወደመ
3.	መድሃኒአለም መጀመሪያ ደረጃ ት/ም/ት ቤት	ሙሉ ለሙሉ የወደመ

ሐ. ድብ ባህር

በተመሳሳይ ሁኔታ አሸባሪው የህወሃት ቡድን በርካታ ውድመቶችን በድብ ባህር ያደረሰ ሲሆን ከትምህርት ተቋማት አኳያ ብቻ-

- 3 (ሶስት) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ሙሉ ለሙሉ አውድሟል።ስም ዝርዝራቸውም እንደሚከተለው ቀርቧል።

ተ.ቁ	የትምህርት ቤቱ ስም	የጉዳቱ ሁኔታ
1.	ሱግሱግ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ት ቤት	ሙሉ ለሙሉ የወደመ
2.	በትሉ ማነቂያ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ት ቤት	ሙሉ ለሙሉ የወደመ
3.	ድብ ባህር የመጀመሪያ ደረጃ ት/ት ቤት	ሙሉ ለሙሉ የወደመ

12

አባሪ ሰነድ 1.

Amhara NRS Education Bureau Ten Top War Affectde Schools in Each Zone (First Round)

Waghimera NA Zone		
S.N	School Name	Woreda
1	Sekota Secondary	Sekota Ketema
2	Tsibaya Primary and Middle	Sekota Ketema
3	Wika Primary and Middle	Ziquala
4	Lay Sayina Primary and Middle	Sekota
5	Wileh Primary and Middle	Sekota
6	Misig Secondary	Sekota
7	Medihanialem Primary and Middle	Sekota
8	Kewziba Secondary	Dehana
9	Amidework Secondary	Dehana
10	Seleamba Secondary	Gazigibela

Semen Wollo Zone		
S.N	School Name	Woreda
1	Kobo Secondary	Kobo Ketema
2	Mersa Secondary	Habru
3	Muja Mariam Secondary	Gidan
4	Gashena Secondary	Wadla
5	Dibeko Primary and Middle	Lasta
6	Geregera Primary and Middle	Meket
7	Ahuntegegn Secondary	Angot
8	Woyiniye Primary and Middle	Gubalafto
9	Estayish Secondary	Gazo
10	Bewa Primary	Raya Kobo

Debub Wollo Zone		
S.N	School Name	Woreda
1	Tsehay Mewucha Secondary	Delanta
2	Haiq Secondary	Tewuledere
3	Haiq Kutir 2 Primary and Middle	Tewuledere
4	Werelu Secondary	Worelu
5	Kutaber Secondary	Kutaber
6	Mehonegna Amba Secondary	Kutaber
7	Kabie Primary and Middle	Kutaber
8	Kuaha Primary and Middle	Worelu
9	Guna Primary and Middle	Tenta
10	Worebabo Secondary	Worebabo

Dessie Ketem Admin.		
S.N	School Name	Woreda
1	Hotie Secondary	Dessie Ketema

Oromo NA Zone		
S.N	School Name	Woreda
1	Jara Primary and Middle	Artuma Fursi

Semen Showa Zone		
S.N	School Name	Woreda
1	Mesobit Primary and Middle	Tarmaber

13

2	Etegie Menen Primary and Middle	Dessie Ketema
3	Tigel Fire Primary and Middle	Dessie Ketema
4	Addis Fana Primary and Middle	Dessie Ketema
5	Boru Meda Primary and Middle	Dessie Ketema
6	Boru Silassie Primary and Middle	Dessie Ketema
7	Segno Gebeya Primary and Middle	Dessie Ketema
8	Tita Primary and Middle	Dessie Ketema
10	Tita Secondary	Dessie Ketema

2	Darensa Primary and Middle	Artuma Fursi
3	Wossen Kurkur Primary and Mi	Julie Tumga
4	Arba Wayu Primary and Middle	Julie Tumga
5	Seritie Primary and Middle	Dewa Chefa
6	Toleha Primary and Middle	Dewa Chefa
7	Sokokie Primary and Middle	Dewa Chefa
8	Derka Primary and Middle	Dewa Chefa
10	Haro Primary and Middle	Dewa Harewie

2	Ataye Secondary	Eferata Gedim
3	Bergibi Primary and Middle	Eferata Gedim
4	Efeson Kutir 1 Primary and M.	Eferata Gedim
5	Karakore Primary and Middle	Eferata Gedim
6	Dejazimach Tesema Erigetie Se	Showa Robit
7	Gadilober Secondary	Eferata Gedim
8	Robit Secondary	Showa Robit
10	Yelen Primary and Secondary	Kewot

Debub Gondar

S.N	School Name	Woreda
1	Nifas Mewucha Secondary	Lay Gayint
2	Nifas Mewucha Pre. Secondary	Lay Gayint
3	Kiraram Primary and Middle	Guna Begemder
4	Gasagn Secondary	Farta
5	Dat Primary and Middle	Esitie
6	Ascha Primary and Middle	Lay Gayint

14

7	Kimir Dengay Primary and Middle	Guna Begemder
8	Gasagn Primary and Middle	Farta
9	Nifas Mewucha Primary and Middle	Lay Gayint
10	Checheho Primary and Middle	Lay Gayint

15

Priority no.	School name	Zone	Wereda	No. of Existing students	Future no of students	Proposed Budget	Name of	Director's Tel.	Wereda education bureau head name	Wereda Education
1	Woama primary and 2ndry school	1	Chifra	249	274	25,68			Mohammed	09127 99410
2	Awra primary and 2ndry school	4	Awra	220	242	2,560	Egah	093 757	Mohammed	09104 1
3	Dersagita primary school	1	Adear	256	282	25,68 7,000			Ali keloyta	09461 85304
4	Bilu primary school	4	Ewa	322	354	4,602			Alhamedu	09207 05193
5	Ususuli primary school	4	Ewa	247	272	3,500			Alhamedu	09207 05193
6	Daraytu primary school	4	Golina	104	115	2,000 ,000			Jemal Roble	09049 05424
7	Hida primary school	2	Megale	351	386	6,400 000			Seid Egahle	09849 99552
8	Arado primary school	2	Megale	277	305	6,400 ,000			Seid Egahle	09849 99552
9	Eligolo primary school	4	Yallo	45	50	5,120			Mohammed	09531 58308
10	Sumsum primary school	1	Chifra	289	318	9,322			Mohammed	09127 99410
11	Galikoma primary school	4	Golina	256	282	4,660			Jemal Roble	09049 05424
12	Askoma primary school	4	Ewa	103	113	1,920			Alhamedu	09207 05193
13	Ala mohammed 2ndry school	4	Eaw	211	232	3,840 ,000. 00			Alhamedu	09207 05193
14	Kelewan primary school	4	Golina	969	1006	7,680			Jemal Roble	09049 05424
15	Wamifage primary school	4	Golina	26	29	3,200			Jemal Roble	09049 05424
16	Warssaye primary school	4	Golina	54	60	3,200			Jemal Roble	09049 05424
17	Dirma primary school	4	Yallo	133	146	3,200			Mohammed	09531 58308
18	Chifra primary school	1	Chifra	2032	2235	1 2,786			Mohammed	09127 99410
19	Mudena primary school	1	Adear	93	102	8,227			Ali keloyta	09461 85304

16

20	Dibena primary school	4	Yallo	129	142	3,200			Mohammed	09531 58308
21	Hariya primary school	4	Awra	64	71	3,200			Mohammed	09103 04131
22	Deraytu primary school	4	Awra	584	642	1,920			Mohammed	09103 04131
23	Alelesubula primary school	4	Ewa	697	769	2,520			Alhamedu	09207 05193
24	Sidahadaba primary school	4	Ewa	97	107	3,200 000			Alhamedu	09207 05193
25	Buti primary school	4	Ewa	110	122	3,840			Alhamedu	09207 05193
26	Gini no 1 ABE	4	Goina	54	60	3,200			Jemal Roble	09049 05424
27	Alena ABE	4	Golina	28	31	3,200			Jemal Roble	09049 05424
28	Gitagile primary school	1	Chifra	98	108	3,200 0,000 .00			Mohammed	09127 99410
29	Bekaru ABE	4	Golina	25	28	3,200			Jemal Roble	09049 05424
30	Kelewan 2ndry school	4	Golina	511	562	1,280			Jemal Roble	09049 05424
31	Lekora primary school	4	Awra	181	199	2,560			Mohammed	09103 04131
32	Hida primary school	4	Awra	324	356	3,840			Mohammed	09103 04131
33	Genu primary school	4	Golina	54	60	2,560			Jemal Roble	09049 05424
34	Mulena assale primary school	4	Golina	128	132	1,280			Jemal Roble	09049 05424
35	Wanasa primary school	4	Golina	44	49	1,280			Jemal Roble	09049 05424
36	Ayga burtele primary school	4	Golina	138	131	1,280			Jemal Roble	09049 05424
37	Gubidora primary school	4	Yallo	499	549	1,160			Mohammed	09531 58308
38	Wekridi primary school	4	Yallo	65	72	1,280			Mohammed	09531 58308
39	Yallo 2ndry school	4	Yallo	299	329	1,280			Mohammed	09531 58308

17

40	Yealo	1	chifra	127	140	3,200			Mohammed	09127 99410
41	Mesgid daba	2	Berahle	94	108	4,500 ,000.			Mohammed hassen	09622 97532
42	Asakach	2	Berahle	197	217	3,200			Mohammed hassen	09622 97532
43	Merkoya	2	Berahle	36	40	3,200			Mohammed hassen	09622 97532
44	Tulena	1	Chifra	111	122				Mohammed	09127
45	Burka	1	Adear	134	147				Ali keloyta	09461
46	Dudula	5	Telalak	124	136	3,200				
47	Kuyes	5	Semurobi	82	90	3,200				
48	Mederakuli	4	Awra	100	110	4,500			Mohammed	09103
49	Hida	4	Awra	323	355				Mohammed	09103
50	Geriro	1	Chifra	416	458	3,200			Mohammed	09127
51	Amuli	1	Chifra	310	341	3,200			Mohammed	09127
52	Assamai	1	Chifra	142	156	4,500			Mohammed	09127
53	Weki	1	Chifra	137	150	3,200			Mohammed	09127
54	Adeledaba	1	Adear	145	160	3,200 ,000. 00			Ali keloyta	09461 85304
55	Midralo ABE	1	Adear	160	176	3,200			Ali keloyta	09461
56	Enika ordi	1	adear	191	210	3,200			Ali keloyta	09461
57	Hayukeli	1	Awra	35	39	3,200			Mohammed	09103
58	Harsimridora	4	Awra	160	176	3,200			Mohammed	09103
59	Burkakomaytu	4	Awra	64	72	3,200			Mohammed	09103
60	Debel	4	Awra	105	126	3,200			Mohammed	09103
61	Artao	4	Ewa	112	123	3,200			Alhamedu	09207
62	Heryabuya	4	Ewa	51	56	3,200			Alhamedu	09207
63	Awelen	4	Ewa	108	119	3,200			Alhamedu	09207
64	Galigube	4	Yallo	45	50	3,200 000			Mohammed	09531 58308
65	Bolotomu	2	Megale	182	200	3,200			Seid Egahle	09849

አባሪ 2.

ወሎ ዩኒቨርስቲ ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ቁሳቁሶች

• Academic & Research Laboratories Facilities • Health and Vet Skill Labs Facilities • Engineering & Technology Workshops Facilities • Computer Labs, informatics labs • Art labs • Language Laboratories • Journalism Studios • Libraries • E-Libraries • Classrooms Facilities • Conference rooms facilities • Seminar rooms and lecture theater Facilities • Training and Pedagogical Centers facilities ICT enhanced Registrar	• Academic & Research Laboratories facilities =732,955,008.82 • Academic and research workshop facilities = 18,066,723.02 • Main and digital library facilities = 100,568,000.00 • Computer lab = 17,075,000.00 • Classrooms and seminar building facilities = 17,376,000 **Sub-total cost = 886,040,731.84**	73.16%	

• Building sanitation damages and destruction • Student Services (Cafeteria, Dormitories, Clinic, dining halls) Facilities • Office furniture • Printing, copier, duplicating machines • LCD projectors • Office computers • Multitasking printing machines • Food items and dining hall furniture • Kitchen & bakery machines • Teacher and student lounge facilities • Generators • Properties in all stores • Spare parts and related items	• Student service (food items, kitchen, clinic and cafeteria) = **60,901,666.51** • Student dormitory facilities = **36,467,240.00** • All office furniture = **33,905,605** • LCD projectors, Printer, Copier, computers, duplicating machines and other electronic equipment = **54,742,995.00** • Teacher and Student Cafeteria Facilities = **1,304,110.00** • Generators and accessories = 80,000,000.00 • Fixed and operating asset stores = **15,954,104.00** Sub Total cost = **283,275,720.51**	23.39%	
3.1. ICT Infrastructures • Router • Switch • Wireless Access Point (AP) • Switch Rack • Fiber Optics • UTP Cable **3.2. Building Infrastructures** • Dining hall (roof, doors and windows) damage • Office, dormitory, classrooms and seminar building doors damage,	**ICT infrastructures** = 17,000,000.00 **Building Infrastructures:-** • Dining hall (roof, doors and windows) damage **= 20,000,000.00** • Office, dormitory, classrooms and seminar building doors damage **= 3,413,597.94** • Office, dormitory, classrooms and seminar building windows damage	3.41%	

• Office, dormitory, classrooms and seminar building windows damage, • Fire extinguisher and fire house,	**= 188,298.69** • **Fire extinguisher and fire house,** **= 752,425.00** **Sub-total cost (ICT and Building infrastructures) = 41,354,321.63**		
• Dairy Farms • Sheep farms • Animal Food items • General Store (Fixed and operating Equipment)	Sheep= 300,000 Animal food items = 250,000 Construction materials = 500,000 **Sub-total = 1,050,000**	0.87%	

ለ. ወልድያ ዩኒቨርስቲ የወደሙ ቁሳቁሶች

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
Academic Areas	• Academic & Research Laboratories Facilities • Health and Vet Skill Labs Facilities • Engineering & Technology Workshops Facilities • Computer Labs, informatics labs • Art labs • Language Laboratories • Journalism Studios • Libraries • E-Libraries • Classrooms Facilities • Conference rooms facilities • Seminar rooms and lecture theater Facilities • Training and Pedagogical Centers facilities	1. College of Medicine and Health Sciences = 344,919,103 2. Faculty of Natural and Computational Sciences (FNCS)= 930,080,423.59 3. Faculty of Business and Economics (FBE)= 26,675,150 4. School of Land Administration (SLA)= 17,708,350.00 5. Faculty of Social Sciences and Humanities = 38,912,800 6. Faculty of Education and Behavioral Sciences (FEBS) = 14,775,185.00 7. Institute of Technology (IOT)= 2,382,508,352 8. College of Agriculture = 206,783,883.30 9. Institute of St. Lalibela Heritage and Truism Studies = 122,356 **10. Libraries=49,500,000.00** 11.Registrar office infrastructure = 36,868,112	74.16%	

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
	• ICT enhanced Registrar	12.Post-Graduate and Academic Program Offices=542,538 13.Class rooms, Lecture Halls and Conference rooms=427,700,000.00 **Sub-total = 4,477,096,252.89**		
Administration Areas	• Office building structural damages • Classrooms, lecture halls building damage & destructions • Water and electric installations • Graduation Hall structural and electromechanical damages • Road and constructions damages • Building sanitation damages and destruction • Student Services (Cafeteria, Dormitories, Clinic, dining halls) Facilities • Office furniture • Printing, copier, duplicating machines • LCD projectors • Office computers • Multitasking printing machines • Food items and dining hall furniture • Modern kitchen & bakery machines • Teacher and student lounge facilities • Vehicles and machinery • Generators • Properties in all stores	1. Generators and Pumps = 135,772,000.00 2. Various types of Vehicles=12,350,000.00 3. Permanent and non-permanent resources in the store = 306,000,000.00 4. Different types of Printers and duplication machines= 33,000,500.00 5. Materials and resources of Students' Cafeteria service = 130,811,895.24 6. Materials and resources of Students and Teachers' Lounge Centers= 4,724,323.50 7. Materials and resources of Students' dormitory services = 333,987,082.00 8. Materials and resources of Students clinic = 5,123,352.00 9. Administrative Offices' Equipment and Resources = 197,057,679.00 **Sub-total = 968,851,831.74**	16.05%	

22

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
	• Spare parts and related items			
ICT and Building Infrastructure	**ICT Infrastructures** • Network/ Server Racks, KVM Switch • Wireless Controller, Wireless LAN, Access Points& with Full Accessories • Structural Cabling System (SCS), Fiber optics lines • Cisco networking academy Lab Bundles • ICT Building Air Conditioning and Security Camera System • Server Room/ Mini-Data Center Uninterruptible Power Supply(UPS) • Cisco Core Enterprise Network and Security • Fiberoptic Splicer Machine and Time Attendance Finger Print Systems • Fiber Cable installation, Power cables, Trunk & Accessories • ICT office Machine Maintenance equipment & Accessories • Inhouse developed and deployed system Software	1. ICT facilities and infrastructures = 38,565,599.80 2. Buildings and constructions = 423,556,143.40 **Sub-total = 462,121,743.20**	7.65%	

23

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
Enterprise Development	• Dairy Farms • Feed processing plants • Enterprise Standard Hotel Furniture, Hotel Sofa, Bakery Machine, Tea-machines, Complete Kitchen devices, Fridge (5) • Enterprise General Store (Fixed Equipment)	1. Dairy Farming=3,328,000.00 2. Leftover processing =40,300,000.00 3. Community service FM Radio 82.9 =85,280,990.60 Sub-total = 128,908,990.60	2.14%	
	Grand total	6,036,978,818.43	100%	

ሐ. መቅደል አምባ ዩኒቨርስቲ

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
Academic Areas	• Academic & Research Laboratories Facilities • Health and Vet Skill Labs Facilities • Engineering & Technology Workshops Facilities • Computer Labs, informatics labs • Art labs • Language Laboratories • Journalism Studios • Libraries • E-Libraries • Classrooms Facilities • Conference rooms facilities • Seminar rooms and lecture theater Facilities • Training and Pedagogical Centers facilities ICT enhanced Registrar	• Academic & Research Laboratories facilities =732,955,008.82 • Academic and research workshop facilities = 18,066,723.02 • Main and digital library facilities = 100,568,000.00 • Computer lab = 17,075,000.00 • Classrooms and seminar building facilities = 17,376,000 **Sub-total cost = 886,040,731.84**	73.16%	

24

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
Administration Areas	• Building sanitation damages and destruction • Student Services (Cafeteria, Dormitories, Clinic, dining halls) Facilities • Office furniture • Printing, copier, duplicating machines • LCD projectors • Office computers • Multitasking printing machines • Food items and dining hall furniture • Kitchen & bakery machines • Teacher and student lounge facilities • Generators • Properties in all stores • Spare parts and related items	• Student service (food items, kitchen, clinic and cafeteria) = **60,901,666.51** • Student dormitory facilities = **36,467,240.00** • All office furniture = **33,905,605** • LCD projectors, Printer, Copier, computers, duplicating machines and other electronic equipment = **54,742,995.00** • Teacher and Student Cafeteria Facilities = **1,304,110.00** • Generators and accessories = 80,000,000.00 • Fixed and operating asset stores = **15,954,104.00** Sub Total cost = **283,275,720.51**	23.39%	
ICT and Building Infrastructure	**3.1. ICT Infrastructures** • Router • Switch • Wireless Access Point (AP) • Switch Rack • Fiber Optics • UTP Cable **3.2. Building Infrastructures** • Dining hall (roof, doors and windows) damage	**ICT infrastructures** = 17,000,000.00 **Building Infrastructures:-** • Dining hall (roof, doors and windows) damage **= 20,000,000.00** • Office, dormitory, classrooms and seminar building doors damage **= 3,413,597.94**	3.41%	


25

Categories	Looted and damaged items	Costs in Ethiopian Birr	Share of categories	Remark
	• Office, dormitory, classrooms and seminar building doors damage, • Office, dormitory, classrooms and seminar building windows damage, • Fire extinguisher and fire house,	• Office, dormitory, classrooms and seminar building windows damage **= 188,298.69** • **Fire extinguisher and fire house,** **= 752,425.00** **Sub-total cost (ICT and Building infrastructures) = 41,354,321.63**		
Enterprise Development	• Dairy Farms • Sheep farms • Animal Food items • General Store (Fixed and operating Equipment)	Sheep= 300,000 Animal food items = 250,000 Construction materials = 500,000 **Sub-total = 1,050,000**	0.87%	
	Grand total	**1,211,152,720.98**	**100%**	

26

አባሪ 11

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ መልስ



የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
አዲስ አበባ / ADDIS ABABA

ቁጥር፣ ፋኢሱ/ባሱዳ/285/2022
ቀን፣ የካቲት 24፣ 2014 ዓ.ም.

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፣ መረጃ ስለመስጠት

ተቋማችሁ ጥር 27 ቀን 2014 በቁጥር ሰመኮ/2.1/50/2014 በዋፈልን ደብዳቤ በትግራይ ክልል ከተከሰተው ግጭት ጋር ተያይዞ በትግራይ ክልል ያለውን ሳይጨምር በአማራ እና በአፋር ክልሎች በሚገኙ ባንኮች ላይ የደረሰውን ውድመት እና ዘረፋ የተመለከተ መረጃ እንዲሰጥ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡ በዚህም አግባብ ከ18 ባንኮች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት፡-

1. በአማራ ክልል በሚገኙ 334 የባንክ ቅርንጫፎች እና በአፋር ክልል በሚገኙ 12 የባንክ ቅርንጫፎች ላይ በግጭቱ ሳቢያ የስራ እንቅስቃሴያቸው ላይ ጉዳት እና መስተጓጎል መፈጠሩ፣
2. የቋሚ ንብረት ጉዳት በአማራ ክልል ብር 552,733,513.40 እንዲሁም በአፋር ክልል ብር 3,215,488.21 መድረሱ፣
3. የጥሬ ገንዘብ ስርቆት በአማራ ክልል ብር 1,606,721,370.14 እንዲሁም በአፋር ክልል ብር 3,250,273.15 መከሰቱ፣
4. ከተሰጠው ብድር ውስጥ በአማራ ክልል ብር 2,790,356,298.75 እንዲሁም በአፋር ክልል ብር 10,454,519.83 የሚሆነው ብድር በግጭቱ ምክንያት የተበላሸ ብድር ውስጥ መግባቱ፣
5. በአማራ ክልል ግምታቸው ብር 110,005,115.15 የሆነ የተለያዩ የንብረት ጉዳቶች መከሰቱ እንዲሁም፣
6. ስድስት የተለያዩ ባንኮች ላይ የተለያየ መጠን ያላቸው የተለያዩ ሀገራት የውጭ ገንዘብ ስርቆት መፈፀሙን ከተሰበሰበው መረጃ ለማረጋገጥ የቻልን መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር


[redacted]
ፍሬዘር አያሌው
ዳይሬክተር፣ ባንኪንግ ሱፐርቪዥን ዳይሬክቶሬት

ግልባጭ፣
- ለክቡር ገዥ
- ለም/ገዥ፣ የፋይናንስ ተቋማት ሱፐርቪዥን
  የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

አድራሻ: ሱዳን ጎዳና፣ P.O.Box 5550/2048 | ፋክስ: +251-11-551-4588 | ስልክ ቁጥር: +251-11-551-7430 | Website:https://nbe.gov.et | SWIFTCODE-NBETETAA

አባሪ 12

ከፌደራል አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የተሰጠ መልስ



በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
DISASTER RISK MANAGEMENT COMMISSION

ቀን 16 የካቲት 2014
Date

ቁጥር ክ2-ወወወ-35/2
Ref.No.

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ምርመራ ግኝቶች ላይ ምላሽ ስለመላክ፣

በርእሱ ስለተጠቀሰው ጉዳይ ጥር 27 ቀን 2014 ዓ.ም በቁጥር ለመክ/2.1/51/2014 በተጻፈ ደብዳቤ በለሚኔ የሀገራችን ክፍል በተፈጠረው ጦርነት ምክንያት በተለይም በአፋርና በአማራ ክልሎች ውስጥ ተፈናቅለው ስለሚገኙ ዜጎች የሰብአዊ አደያዝና የምግብ ዋስትና አቅርቦት ሁኔታ ፣የተፈናቃዮች ቁጥር አሁን ያሉበትን ቦታ እንዲሁም በእርዳታ ስርጭቱ ሂደት ላይ ያጋጠመ· ገደቦች ወይም ክልከላዎች ካሉ የአናንተ ደብዳቤ በደረሰን በሰባት ቀናት ውስጥ ምላሽ እንድንልክ የተጠየቀውን ይመለከታል።

ይሁን እንጂ ከአቅም በላይ የሆኑ የአገሬሽን ሥራዎች ምክንያት መረጃውን በተባለው ጊዜ ገደብ ለማድረስ ባለመቻላችን ይቅርታ እየጠየቅን የተዘጋጀውን ምላሽ ሪፖርት 7 ገጽ ከዚህ ጋር አያይዘን መላካችንን በትህትና እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር
[redacted]
ነሲቡ ያሲን ሰይድ
ምክትል ኮሚሽነር

እንዲያውቁት
- ለክቡር ኮሚሽር
  ኢ/ያ/ኢ/ክ

ግልባጭ
- ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክተሬት
  ኢ/ያ/ኢ/ክ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
ዋና ኮሚሽነር


ፋክስ ቁጥር 0115514788
Fax No. 0114424974

ፖ.ሳ.ቁ.
P.O.Box 5686
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ/ Addis Ababa -Ethiopia
website: www.dppc.gov.et

ስልክ ቁጥር 0115-524259
Tel. No. 0115-524272
0114-424966

አባሪውን መልስ ሲሰጡ የደብዳቤያችንን ቁጥር ይጥቀሱ

Please quote Our Ref. No. When replynig



ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ለአደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የቀረቡ ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች ፡-

አጠቃላይ

- በግጭቱ አካባቢዎች ስለአለው የሰብአዊ ድጋፍ፣ተደራሽነትና የሰብአዊ ሁኔታዎች በምግብ አቅርቦት ረገድ ምን ይመስላል ፡
- በአማራና አፋር ክልሎች በተካሄዱ ውጊያዎች የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ብዛትና ሁኔታ፣የሚገኙበት ቦታ ፣ለተፈናቀሉ ነዋሪዎች ስለተደረገ ሰብአዊ ድጋፍ ፤
- በግጭቱ አካባቢዎች ስለአለው የሰብአዊ ድጋፍ፣ተደራሽነት ፣ገደቦችና ክልከላዎች

ስለ አገር ውስጥ ተፈናቃዮች

- በግጭቱ አካባቢዎች ስለሚኖሩ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሁኔታና ተፈናቃዮችን ወደ መኖሪያቸው ለመመለስ ና ለማቋቋም ስለተከናወኑ ተግባራት ፤-
- በቂ የሰብአዊ ድጋፍ አለመቅረብና የእርዳታ ተደራሽነት ላይ የተጣሉ ገደቦችን በሚመለከት የተደረገ ማጣራትና የተወሰደ እርምጃ ፤-

በግጭቱ አካባቢዎች ስለአለው የሰብአዊ ድጋፍ፣ተደራሽነትና የሰብአዊ ሁኔታዎች በምግብ አቅርቦት ረገድ ምን ይመስላል፣

1. በአማራ ክልል

1.1. የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነት ሁኔታ፤-

በክልሉ የአለው የሰብአዊ ድጋፍ ስራ የተከናወነው ከአማራ ክልል አደጋ ስጋትና ምግብ ዋስትና ቢሮ በክልሉ ውስጥ 11,641,554 የሆኑ ነዋሪዎች በጦርነቱ ምክንያት የምግብ ክፍተት ያለባቸው መሆኑን ባሳወቀው መሰረት ነው ። በወቅቱ በነበረው የጸጥታ ሁኔታ ምክንያት የጸሰላ ጥናት በማካሄድ ትክክለኛውን የተረጅ ቁጥር መለየት ባለመቻሉ የሰው ሕይወት በምግብ እጥረት እንዳያልፍ በማሰብ ለጊዜው ክልሉ ያቀረበውን የተረጅ ቁጥር በመቀበል ድጋፉ ሲቀርብ ቆይቷል ። በክልሉ የምግብ ክፍተት ያለባቸው ወገኖች መረጃ ቀጥሉ ተመልክቷል ።

1

ሰንጠረዥ "ሀ" በክልሉ የምግብ ክፍተት ያለባቸው ወገኖች መረጃ

ተ.ቁ	ዞን	ነባር ተፈናቃይ	በጦርነቱ የተፈናቀሉ	ሌሎች እርዳታ ፈላጊዎች	ድምር	መግለጫ
1	አዊ	46,215	----	2,695	48,910	
2	ማዕ/ጎንደር	28,541	2,730	194,177	225,448	
3	ምስ/ጎጃም	33,310	695	17,476	51,481	
4	ሰ/ጎንደር	42,651	133,916	804,581	981,148	
5	ሰ/ሸዋ	271,102	441,650	310,208	1,022,960	
6	ሰ/ወሎ	23,975	167,000	1,682,355	1,873,330	
7	ኦሮሞዞን	109,334	-------	490,587	599,921	
8	ደ/ጎንደር	50,759	77,069	2,146,813	2,274,641	
9	ደ/ወሎ	23,318	291,016	3,073,046	3,387,380	
10	ዋግህምራ	5,786	71,089	607,888	684,763	
11	ወልቃይት ጠገዴ		190,739	-	190,739	
12	ምዕ/ጎጃም	281,446	35409	17,045	299,810	
13	ምዕ/ጎንደር	1,567		-544	1,023	
	ድምር	918,004	1,411,313	9,312,237	11,641,554	

ከላይ በሰንጠረዥ "ሀ" ላይ እንደተመለከተው የምግብ ክፍተት ካለባቸው 11.6 ሚሊየን ወኖች ውስጥ በክልሉ የነበረው 1,411,313 አዲስ የተፈናቃይ ቁጥር የተካተተ ነው ። በመሆኑም በተከበረው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ከተጠየቀው ጥያቄ አነጋ ምላሽ የምንሰጠው ለጠቅላላው 2,329,317= (ነባር 918004+ አዲስ 1,411,313) ተፈናቃይ ሳይሆን በጦርነቱ ምክንያት አዲስ የተፈናቀሉትን 1,411,313 ወገኖች በተመለከተ ነው።

ሰንጠረዥ "ለ" በክልሉ በጦርነት ምክንያት የተፈናቃይ ቁጥር መረጃ በየዞኑ

ተ.ቁ	ዞን	በጦርነቱ	መግለጫ
1	ሰሜን ሸዋ	441,650	
2	ሰሜን ወሎ	167,000	
3	ወልቃይት ጠገዴ	190,739	
5	ማዕከላዊ ጎንደር	2,730	
6	ደቡብ ወሎ	291,016	
8	ባህር ዳር	35,409	
10	ዋግኽምራ	71,089	
11	ምስራቅ ጎጃም	695	
12	ሰሜን ጎንደር	133,916	
13	ደቡብ ጎንደር	77,069	
	ድምር	1,411,313	

ከእነዚህ ተፈናቃዮች መካከል በህግ ማስከበር ሂደት የሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ልዩ ዞን፣ የደቡብ ወሎ እና የሰ/ወሎ ዞን ሙሉ በሙሉ እንዲሁም የዋግህምራ ዞን በአብዛኛው ከጦርነቱ ነጻ በመውጣታቸው በፌደራልና በክልሉ መንግስት አስተባባሪነት እና በተፈናቃቹ ፍላጎትና ስምምነት 1,277,397 ተፈናቃዮች ወደ ቀድሞ አካባቢቸው ተመልሰዋል ።

በሌላ በኩል የነበሩበት አካባቢቸው የጸጥታ ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ እንዲሁም በአማራና በትግራይ አዋሳኝ አካባቢ በነበረው ጸግም ትንኮላ ምክንያት ከአካባቢያቸው አቅራቢያ የተሰባሰቡ ወገኖችን ጨምሮ በየካቲት ወር 2014 ዓም የመጀመሪያ ሳምንት በክልሉ 247,466 ተፈናቃዮች የሚገኙ ሲሆን ዝርዝሩ በሰንጠረዥ "ሐ" ቀጥሎ ተመልክቷል ።

ሰንጠረዥ "ሐ" በአሁኑ ጊዜ በክልሉ በጦርነት ምክንያት ተፈናቅለው የሚገኙ ተፈናቃዮች ብዛትና የሚገኙበትን ቦታ የሚያሳይ መረጃ

ተ.ቁ	ዞን	ከተማ	የተፈናቃይ ብዛት	በተፈናቃይ ጣቢያ ውስጥ ያሉ	በማህበረሰቡ ውስጥ ተጠልለው ያሉ
1	ሰሜን ሸዋ	ደብረ-ብርሃን	44,777	10,142	34,635
2	ሰሜን ወሎ	ቆቦ	34,560	34,560	
3	ደቡብ ወሎ	መካነ ሰላም	1,225	1,225	
	ዋግ ኽምራ	ሰቆጣ	23,371	9,005	23,983
4		ዝቋላ	9,617		
5	ሰሜን ጎንደር	ደባርቅ እና ዳባት	133,916	5,206	128,710
	ድምር		247,466	60,138	187,328

ከ247,466 የተፈናቃይ ቁጥር 113,550 ተፈናቃዮች በዳግም ትንኮሳ በድጋሚ የተፈናቀሉ ናቸው ።

1.2. **የድጋፍ አቅርቦትን በተመለከተ፤-**

- በክልሉ በተፈጠረው የእስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ምክንያት የጦርነቱ ሰለባ ለሆኑ የህ/ሰብ ክፍሎችና ተፈናቃዮች ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች ሲደረጉ ቆይተዋል ።የድጋፍ አሰጣጡም ቅድሚያ በመጠለያ ጣቢያ ለተሰባሰቡና በማሕበረሰቡ ውስጥ ተጠግተው ለነበሩ ተፈናቃዮች ቅድሚያ በመስጠት ነው።
- በእዚህም መሰረት እስከ ጥር 28/2014 ዓም ድረስ ለ8,803,572 በጦርነቱ ምክንያት ድጋፍ የሚፈልጉና የተፈናቀሉ ወገኖች በመንግስትና በአጋር ድርጅቶች ትብብር 1,478,911 ኩንታል የምግብ እህል ተሰራጭቷል ።
- የድጋፍ አቅርቦቱ በመንግስትና በአጋር ድርጅቶች አማካኝነት የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከእዚህ እንደሚከተለው ነው ።
  - ✓ በመንግስት 666,947 ኩንታል የምግብ እህል ለ4,443,313 ተፈናቃዮች ፤አቅርቧል

- ✓ በጆኦፕ/ በክርሲቲያና ተራድኦ ድርጅት/ 595,497 ኩንታል የምግብ እህል ለ3,379,111 ለሆኑ ተፈናቃዮች አቅርቧል ፤
- ✓ በዓለም የምግብ ፕሮግራም በኩል 216,917 ኩንታል የምግብ እህል ለ 981,148 ለሚሆኑ ተፈናቃዮች አቅርቧል ።


ከዚህም በተጨማሪ፦

- ✓ መንግሥት ለተፈናቃዮች የመጠለያ፣ የአልባሳትና የመጠለያ ቁሳቁስ አቅርቧል።
- ✓ ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ወገኖች በጋራና በተናጠል የበሰለ ምግብ በማቅረብ የተፈናቃይ ወገኖችን ህይወት ለመታደግ ተችሏል ።
- ✓ ክልሎች ፤ባለሃብቶች ፤ማህበራት ፤የግልና የመንግስት ድርጅቶች ወዘተ...ለተፈናቃይ ወገኖች ያለይነትና የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል ።

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የሚሰጠው ሰብአዊ ድጋፍ ለተፈናቃይ ወገኖች የቅድሚያ ትኩረት በማድረግ ሲሆን በወቅቱ ከተፈጠረው ችግር አኳያ በተለይ በወረራ በተያዙ አካባቢዎች የሚገኘው ህብረተሰብ የራሱን የምግብ ፍላጎት የሚሸፍንበት አማራጭ /የባንክ አገልግሎት ፤የገበያ አቅርቦት ወዘተ.../ እንደሌለው በመታመኑ ሁሉንም ወገን ያማከለ እንዲሆን ተደርጓል። የድጋፍ አቅርቦት መረጃ ከላይ በተ.ቁ በ1.2 ላይ ለማሳየት ተሞክሯል ።

1.3. **በግጭቱ አካባቢዎች ስለአለው የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነት ፤ገደቦችና ክልከላዎች፤**

- በፌደራልም ሆነ በክልሉ መንግስት ደረጃ ድጋፍ ለሚፈልጉ ወገኖች አርዳታ እንዳይደርስ የተደረገ ክልከላ የለም ።
- በአንጻሩ ግን በጸጥታ ችግር ምክንያት በአሸባሪው ህውሓት ተይዘው በቆዩባቸው በዋግህምራ እና በሰ/ወሎ ዞኖች ውስጥ የሚኖሩ ወገኖች ከ3-5 ለሚደርሱ ወራት ድጋፍ ሳያገኙ ቆይተዋል ። መንግስት ለእነዚህ ወገኖች እርዳታ ማቅረብ የሚችሉ አጋር አካላትን ሲያስተባብር የቆየ ቢሆንም በጸጥታው ምክንያት የሚጠበቀውን ያህል ሊሳካ አልቻለም ። በተመሳሳይ መልኩም በደቡብ ወሎ፤በአርሮሞ ዞን ፤በሰሸዋ በወራሪው ሃይል በተያዙ ቦታዎች የእርዳታ አቅርቦቱ ተስተጓጉሎ ነበር ።
- ከላይ የተጠቀሱት አካባቢዎች ከወራሪው ሃይል ነጻ ከወጡበት ጊዜና ዕለት ጀምሮ እርዳታው በመንግስትና በአጋር ድርጅቶች እየቀረበ እስካሁንም ድረስ ይገኛል ።
- ይህ በእንዲህ እያለ ወራሪው ሃይል በአማራና በትግራይ አዋሳኝ አካባቢዎች (አበርገሌ፤ጻግቢጂ፤) በሚያደረገው ትንኮሳ ምክንያት እርዳታ ማቅረብ እየተቻለ አይደለም ።



- የወራሪው ሃይል በፈጠረውና በሚፈጥረው ትንኮሳ ምክንያት አርዳታ የማያገኙና ወደ ሰላማዊ ቦታ መንቀሳቀስ ለሚችሉ ወገኖች በቅርብ አርቀት አርዳታ ማግኘት እንዲችሉ መንግስት ሊያመቻች ቆይቷል ፤ አሁንም እየመቻች ይገኛል ።

2. አፋር ክልል

በግጭቱ አካባቢዎች ስለአለው የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነትና የሰብአዊ ሁኔታዎች በምግብ አቅርቦት ረገድ ምን ይመስላል።


2.1. የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነት ሁኔታ፤-
በክልሉ የምግብ ክፍተት ያለባቸው ወገኖች መረጃ፣

- በአጠቃላይ1.3 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ አስቸኳይ የምግብ አርዳታ የሚያስፈልገው ነው፤ በክልሉ በጦርነቱ ምክንያት ከ 21 ወረዳዎች ከ400,000 በላይ ህዝብ ከመኖሪያ አካባቢው ተፈናቅሉ ቆይቷል።

በጥር ወር 2014 ዓም መጨረሻ የትግራይ ወራሪ ሃይል የአፋር ክልልን መልሶ ለማጥቃት ባደረገው ወረራ 294,400 የሚሆኑ ዜጎች በአዲስ መልክ ከበረሃሌ ፤ቆኖባ፤ ባላ፤ምጋል፤ኢራቡቲ ከተባሉ ወረዳዎች ላይ ተፈናቅለዋል ።፤ ገርጋሪም በሰንጠዝ መ ተመልክቷል ።
በመሆኑም ከክልሉ በተገኘው መረጃ በክልሉ የሚገኙው የተፈናቃይ ቁጥር ከ694,400 በላይ ከፍ ብሎ ታይቷል።

ሰንጠረዥ "መ" በጥር ወር 2014 ዓ.ም የተፈናቀሉ ወገኖች የሚገኙበት ቦታና የተፈናቃዮች ቁጥር መረጃ፣

ተ.ቁ	ዞን	ከተማ	የተፈናቃይ ብዛት	በተፈናቃይ ጣቢያ ውስጥ ያሉ	በማህበረሰቡ ውስጥ ተጠልለው ያሉ
1	ኪልበትቲ(ዞን 2)	ዲርማ	32,136	✓	
		ዳዑራ	65,585	✓	
		ሃመድኢላ	53,590	✓	
		በለልበሳና ለሳጋዲ	66,848	✓	
		ገርበና	66,172		
		አዙላሥ	10,069	✓	
		ድምር	294,400		



2.2. የድጋፍ አቅርቦትን በተመለከተ የተሰጠ ድጋፍ፤-

- ቀደም ሲል የተፈናቀሉ ከ400 ሺ በላይ ወገኖችን ጨምሮ በክልሉ የምግብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው 1.3 ሚሊየን ወገኖች በመንግሥትና በተለያዩ በጎ አድርጊ አካላት 90,856 ኩንታል ምግብ ተሰራጭቷል እየተሰራጨም ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ በቅርቡ ሰተፈናቀሉትና በ6 ወረዳዎች ውስጥ ለሚገኙት 294,400 ወገኖች 25,291 ኩንታል ምግብ 17,760 ካርቶን ብስኩትና 6,132 ካርቶን ቴምር ተሰራጭቷል። አሁንም የስርጭቱ ሥራ ቀጥሏል።

በቅርቡ የተሰራጨ ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን በተመለከተ፤-

- በመጠለያ እና ቁሳቁስ ረገድም በመንግስት 9,300 ብርድ ልብስ፣ 3,650 ምንጣፍ ፣ 3,428 ሽራ፣ ጁንካን 25 በቁጥር፣ ብረት ድስት 500 በቁጥር፣ የውሃ ኮባያ 1500 በቁጥር፣ ሶላር 564 በቁጥር እና 175 አስር በጎዳ ልብስ ለ5 ወረዳዎች ተሰራጭተዋል።
- የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር ለ 2,000 አባወራ መጠለያ እና ቁሳቁስ አሰራጭቷል። ANE የተባለ ሲጋሽ ድርጅት ለ750 አባወራ መጠለያ እና ቁሳቁስ አሰራጭቷል።
- World Vision የተባለ ሲጋሽ ድርጅት 1250 አባወራ መጠለያ እና ቁሳቁስ አሰራጭተዋል። አጠቃላይ በመጠለያ እና ቁሳቁስ 25800 የሚሆኑ ሰዎች ተደራሽ ማድረግ ተችሏል።
- በውሃ ሳኒቴሽን ረገድም ከአፋር አደጋ መከላከል 2 የውሃ ቦቲ ፣ 200 ጀርካን ፣ 15 የውሀ ሮቶ እና 21,528 በቁጥር ሀይላንድ ውሀ ድጋፉ ተደርጓል።

2.3. በግጭቱ አካባቢዎች ስለአለው የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነት ፤ገደቦችና ክልከላዎች

- በፈደራልም ሆነ በክልሉ መንግስት ደረጃ ድጋፍ ለማፈልጉ ወገኖች አርዳታ እንዳይደርስ የተደረገ ክልከላ የለም ።
- በአንጻሩ ግን በጸጥታ ችግር ምክንያት በአሸባሪው ህውሓት በተያዙ ቦታዎች የተወለኑ ወረዳዎች ለጥቂት ወራት ድጋፍ ሳያገኙ ቆይተዋል ።
- መንግስት ለእነዚህ ወገኖች አርዳታ ማቅረብ የሚችሉ አጋር አካላትን ሲያስተባብር የቆየ ቢሆንም በክልሉ ውስጥ የጸጥታው ችግር እየሰፋ መሞቱ በክልሉ አምስት ወረዳዎች ያህል በትግራይ ወራሪ ሃይል የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነት ፤ገደቦችና ክልከላዎች የተደረጉባቸው አካባቢዎች አሉ ።

ባጠቃላይ በፈዴራልና በክልል መስተዳድሮች አስተባባሪነት እና በአጋር ድርጅቶች ተሳትፎ በጦርነት ምክንያት ሰተፈናቀሉ ወገኖች ትኩረት ተሰጥቶ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን እንገልጻለን።